# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የአገሪቱን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ለማስተባበር ለመጀመሪያ ጊዜ በ1968 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 62/1968 ኮሚሽን በሚል ስያሜ ተቋቋመ፡፡ በቀጣይነትም በ1986 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 91/1986 እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ የአስፈፃሚ መ/ቤቶችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 ኮሚሽኑ የቀድሞ ስያሜውን ትቶ ኤጀንሲ ተብሎ እንዲጠራ ተደርጓል፡፡ በቀጣይነትም በ2001 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 604/2001 ኤጀንሲው ወደ ሚኒስቴር ደረጃ እንዲያድግና ተጠሪነቱም ለሚኒስቴሮች ም/ቤት እንዲሆን ተደርጓል፡፡
2. የቆላ ዝንብ ከሰሃራ በታች ባሉ 37 የአፍሪካ ሀገሮች ተሰራጭቶ የሚገኝ ሲሆን 23 ያህል ዝርያዎች ተለይተው የታወቁ መሆኑ ተገልጿል፡፡ እነዚህ የቆላ ዝንብ ዝርያዎች በሰው ላይ በአፍሪካ የእንቅልፍ በሽታ /sleeping sickness/ እንዲሁም በእንስሳት ላይ ገንዲ /naganeng/ የተባሉትን በሽታዎች በማስተላለፍ ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ በማድረስ ላይ መሆናቸው ተገልጿል፡፡
3. በኢትዮጵያም የቆላ ዝንብ ባለበት አካባቢ ሰፍረው የሚኖሩ ህዝቦችም በዚሁ በቆላ ዝንብ በሚተላለፈው የገንዲ በሽታ ምክንያት የቀንድ ከብቶቻቸውና ሌሎች የቤት እንስሳቶቻቸው ምርታማ ሊሆኑ ባለመቻላቸው ያላቸው የእንስሳት ሀብት ሊኖራቸው ከሚችለው ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ከእንስሳት ሀብት የሚያገኙት ውጤትም እንደዚሁ ከሚጠበቀው በታች መሆኑ በጥናት ሰነዶች ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም የቀንድ ከብቶችን በመጠቀም በአካባቢው የእርሻ ልማት ለማካሄድ የሚደረገውን ጥረት በሽታውን የሚያስተላልፈው የቆላ ዝንብ መኖሩ የእርሻ ከብቶች ለገንዲ በሽታ መጋለጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድርሶበታል፡፡
4. የገንዲ በሽታን ለመቆጣጠር በአገራችን የተለያየ ጥረት ሲደረግ የቆየ ቢሆንም፣ ጥረቶቹ በአብዛኛው ያተኮሩት ለበሽታው መፈወሻ የሚሆን መድሀኒት በመጠቀም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት መድሀኒቶቹ ለረዠም ጊዜ በጥቅም ላይ በመዋላቸውና አልፎ አልፎ በአግባቡ በጥቅም ላይ ባለመዋላቸው በአንዳንድ አካባቢዎች በሽታው መድሀኒቶቹን የመላመድና የመቋቋም ሁኔታ በማሳየት ላይ ይገኛሉ፡፡

5. በመሆኑም በሽታውን በመድሀኒት ከመቆጣጠር በተጨማሪ የበሽታው አስተላላፊ የሆነውን የቆላ ዝንብ ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘዴ ተግባራዊ ተደርጐ ቆይቷል፡፡ ይህም ዘዴ በአመዛኙ የዝንቧን ብዛት በፀረ ዝንብ ኬሚካል የመቀነስ አካሄድ ሲሆን፤ በተወሰኑ ቦታዎች ደግሞ የዝንብ ወጥመድ (Trap) በመጠቀም ጭምር ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው እስካሁን ለረዥም ጊዜያት የተሰሩት ስራዎች በበሽታውም ሆነ በሽታውን በምታስተላልፈው ዝንብ ላይ የተወሰዱት እርምጃዎች በቁጥጥር ላይ እንጂ በማጥፋት ላይ ያላተኮሩ እንደነበሩ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተገኙ ሰነዶች እና መግለጫዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
6. ከዚህም በመነሳት የገንዲን በሽታና አስተላላፊ የሆነውን የቆላ ዝንብ ለማስወገድ የሚያስችል ነፍሳትን የማምከን ቴክኖሎጂ በተለያዩ የሰሜንና መካከለኛው አሜሪካ፣ በእስያ እንዲሁም በሰሜንና ምስራቅ አፍሪካ የፍራፍሬ ተባይና የእንስሳት በሽታ አስተላላፊ የሆኑ ዝንቦችን ለማጥፋት በሚደረግ ጥረት ላይ ተግባራዊ ሁነው ውጤታማነቱ ተረጋግጧል፡፡
7. በመሆኑም ይህን አዲስ ቴክኖሎጂ ስራ ላይ ለማዋልና በሀገራችንም የቆላ ዝንብን ለማጥፋት በሚያስችል ነፍሳትን የማምከን ቴክኖሎጂ (The Sterile Insect Technique) አጠቃቀም አቅም በብሔራዊ ደረጃ ለመገንባትና በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ 25,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ቦታ ከገንዲ በሽታ እና ቆላ ዝንብ ነፃ ለማድረግ የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት በ1990 ዓ.ም በኢትዮጵያ መንግስትና በአለም አቀፍ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ መካከል በተደረገ የጋራ ስምምነት ተቋቁሞ የቆላ ዝንብን ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት 10 ዓመታት ድረስ ለማጥፋት ኘሮጀክት ተቀርጾ ትግበራ ላይ የሚገኝ ነው፡፡
8. ኘሮጀክቱም ለአገራችን በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን የነፍሳት ማምከን ቴክኖሎጂን ሥራ ላይ በማዋል በአጠቃላይ በአገሪቱ የቆላ ዝንብ ከሚገኝበት 240,000 ካሬ.ኪ.ሜ ውስጥ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የሚገኘውን 25,000 ካሬ.ኪ.ሜ ስፋት ያለው መሬት እንደገና ከ2003-2007 ባለው ጊዜ ውስጥ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሙሉ በሙሉ ነፃ ለማድረግ የሚያስችለውን የአሰራር ሂደት በሐምሌ 2002 ዓ.ም በመቅረፅና ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## የፕሮጀክቱ ራዕይና ተልዕኮ

### ራዕይ

9. የሳይንሳዊ ምርምር ውጤት የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን አቀናጅቶ ሥራ ላይ በማዋል አገራችን ከቆላ ዝንብ እና ከገንዲ በሽታ ነፃ ሆና ማየት፣

### ተልዕኮ

10. በቆላ ዝንብና በገንዲ በሽታ ምክንያት ሊለማ ያልቻለውን ሰፊና ለም መሬት የተቀናጀና ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከችግሩ ነፃ በማድረግ ሀገራችን ቢያንስ በአጭር ጊዜ ውስጥ በምግብ ሰብል ራሷን እንድትችል በማድረግ መንግስት ያወጣውን የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ማገዝ፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

11. ከጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባራት መካከል ጽ/ቤቱ፡-

- በፕሮጀክቱ ዶክመንቱ ላይ የተጠቀሰውን ዕቅድ መነሻ መሰረት በማድረግ፤ ከፕሮጀክቱ ክልላዊ ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና ከቆላ ዝንብ ማራቢያና ማምከኛ ማዕከል ጋር በመሆን፣ የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ዓመታዊና ወርሃዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ለኮሚሽኑ አቅርቦ ያፀድቃል፤ የፀደቀውን የፊዚካልና ፋይናንሻል ዕቅድ ለክልል አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ለክልሉ ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ፣ ለክልሉ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና ለቆላ ዝንብ ማራቢያና ማምከኛ ማዕከል ማሳወቅ፣
- ከክልል ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ጋር በቅርብ በመስራትና ከክልሉ ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ጋር ግንኙነት በመፍጠር የፕሮጀክቱ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ በወጣው ዝርዝር የስራ ዕቅድና ፕሮግራም መሰረት መከናወኑን በየወሩና በየሩብ ዓመት ከክልሉ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት በሚደርሱት ሪፖርቶች መሰረት ይከታተላል፣ ይገመግማል፤ አስፈላጊ የሆኑ የማጠናከሪያ እርምጃዎች የሚወሰዱበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- ለፕሮጀክቱ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል በፕሮጀክቱ የሰው ኃይል ፍላጎት ላይ በመመርኮዝ በብሔራዊ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት፣ በክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት፣ በመስክ ኦፕሬሽን ቡድኖችና በቆላ ዝንብ ማራቢያና ማምከኛ ተቋም

መሟላቱን ይከታተላል፤ በተለያዩ ምክንያት በሚለቁ ሠራተኞች ምትክ በሲቪል ሰርቪስ ሕግና ደንብ መሠረት በለቀቁት ምትክ ወዲያው መተካቱን ይከታተላል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ የስራ መደቦች እንዲፈቀዱ ይጠይቃል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፣

- ብሔራዊና ክልላዊ የሆኑ ከገንዲና ከቆላ ዝንብ ጋር የተዛመዱ ምርምር የሚያከናውኑ ተቋማት በፕሮጀክቱ በመሳተፍ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉበትንና እነሱም በሚያደርጉት ተሳትፎ አቅምና ልምዳቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉበትን መንገድ በማጥናትና ሀሳቡን ለኮሚሽኑና ለዓለም አቀፍ የአቶሚክ ኃይል ድርጅት በማቅረብ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ከሚኒስቴሩና ከክልሉ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር በመሆን ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆኑ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች በወቅቱ ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት፣ ከፕሮጀክቱ ሠራተኞች ውጭ ከፕሮጀክቱ አካባቢ የሚቀርቡ የስልጠና ፍላጎቶች ለፕሮጀክቱ ሥራ ከሚኖራቸው ጠቀሜታ አኳያ ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- ለፕሮጀክቱ ተግባራት መቃናትና ውጤታማ መሆን የሚያስፈልጉ አጠቃላይ የአፈፃፀም መመሪያዎችንና ደንቦችን ማዘጋጀት፤ ማፅደቅ፤ አፈፃፀማቸውን መከታተል፤ እንዳስፈላጊነቱ እንዲሻሻሉ ማድረግ፣
- የፕሮጀክቱን ዕቅድ፣ ፕሮግራም፣ ስትራቴጂና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለብሔራዊ ፕሮጀክት አስተባባሪ ኮሚቴና ለብሔራዊ ፕሮጀክት የቴክኒክ አማካሪ ቡድን አዘጋጅቶ ማቅረብ፣ የኮሚቴዎቹ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት፣ ተግባራዊነታቸውን መከታተል፣
- ከፕሮጀክቱ ውጪ በሆኑ አጎራባች አካባቢዎች ለሚደረገው የቆላ ዝንብ ቁጥጥር ፕሮግራም የሰው የኃይልና የማቴሪያሎች ድጋፍ እንዲሰጥ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ከአለም አቀፍ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ የሚመጡ የአጭርና ረጅም ጊዜ ድጋፍ ሰጪ ኤክስፐርቶችን ሥራ ማስተባበርና መከታተል፣

ናቸው፡፡

## የፕሮጀክቱ አደረጃጀት

12. ፕሮጀክቱ በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን፣ በስሩ (አዋሳ የክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የሚገኝና በዚህ ስር 3 ጣቢያዎች/ወላይታ ሶዶ፣ አርባ ምንጭ እና ዲላ) ያሉትና ተጠሪነቱም ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሲሆን፣ በሶስት ዋና የስራ ሂደቶች (የቆላ ዝንቦች ለማጥፋት የሚያስችል የአቅም ግንባታ፣ የመስክ ኦፕሬሽን እና የተቀናጀ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቆላ ዝንብን የማጥፋት ዋና የስራ ሂደቶች) እና በስድስት ደጋፊ የስራ ሂደቶች (የሰው ሀብት ስራ አመራር፣ የፋይናንስ፣ አቅርቦትና ንብረት አስተዳደር፣ የፕላንና ፕሮግራም፣ የውስጥ ኦዲት እና ህዝብ ግንኙነት ደጋፊ የስራ ሂደቶች) የተደራጀ ነው፡፡

## የፕሮጀክቱ የሰው ሀይል

13. ለፕሮጀክቱ በአጠቃላይ 288 የሥራ መደቦች የተመደቡ ሲሆን ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ 163 ሰራተኞች ሲኖሩት ከዚህ ውስጥ 111 ድጋፍ ሰጪ/support/ እና 52/Technical/ ሠራተኞች ይገኙበታል፡፡

## የፕሮጀክቱ የፋይናንስ ምንጭ

14. ፕሮጀክቱ ከመንግስት፣ ከአፍሪካ ልማት ባንክ እና ከአለም አቀፍ የአቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ድጋፍ የሚደረግለት ሲሆን፤ ከ2001-2003 ከመንግስት ከተመደበለት በጀት ውስጥ፤
    - በ2001 ዓ.ም ብር 14,541,214 ተመድቦ፤ ብር 9,126,571 ወጪ ሆኗል
    - በ2002 ዓ.ም ብር 19,639,540 ተመድቦ፤ ብር 7,298,562 ወጪ ሆኗል
    - በ2003 ዓ.ም ብር 18,496,253 ተመድቦ፤ ብር 11,357,010 ወጪ ሆኗል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

15. የደቡብ ኢትዮጵያ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት የቆላ ዝንብን እና የገንዲ በሽታን የማጥፋት ሂደት ብቃት ባለው መንገድ የሚያከናውንና ወጪውም ቁጠባን ያገናዘበና አላማውንም ስኬታማ ማድረጉን በማጣራት የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳቦችን (Recommendations) ለመስጠት እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

**<u>የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ እና ጭብጥ</u>**

16. ከላይ እንደተገለጸው የኦዲቱ ዓላማ በፕሮጀክቱ ሊከናወን የታቀደው የቆላ ዝንብን የማጥፋት ሥራ ሂደት ውጤታማነት ላይ ሲሆን፤ ይህንኑ የኦዲት ዓላማ ለማሳካት ሁለት የኦዲት አቅጣጫዎች(Issues) እና ሶስት ንዑስ የኦዲት ጭብጦች(Sub Issue) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-
    - ፕሮጀክቱ በተዘጋጀለት እቅድ መሠረት ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው መንገድ መከናወኑንና አላማውን ስኬታማ ማድረጉን ማጣራት፣
        - ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባዘጋጀው ዕቅድ መሰረት መስራቱን እና የአሰራር ስርዓቱ ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፣
        - ✓ የፕሮጀክቱን ሥራ ቀልጣፋ ለማድረግ የሚያስችል የግዢ ሥርዓት፣ የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መኖሩን በተመለከተ፣
        - ✓ ለፕሮጀክቱ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣
    - የፕሮጀክቱ ሥራ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ሕብረተሰብ የቆላን ዝንብ ለማጥፋት የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲያገኝ ስለመደረጉና የባለድርሻ አካላት ተሣታፊ ስለመሆናቸው ማጣራት፣

    የሚሉ ናቸው፡፡

**<u>የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/</u>**

17. ለተመረጠው የኦዲት አቅጣጫ/ጭብጥ/ 44 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን የመመዘኛ መስፈርቶቹም ዝርዝር ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

**<u>የኦዲቱ ወሰንና ዘዴዎች</u>**

18. ኦዲቱ የሚሸፍነው ቀደም ብሎ የተሞከሩትን አሠራሮች ጨምሮ ከ2001 በጀት ዓመት ጀምሮ የኦዲት ሥራው እስከሚጠናቀቅበት በጀት ዓመት ድረስ ያለውን የቆላ ዝንብ የማጥፋት እንቅስቃሴን ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት ላይ ሲሆን፤ የቆላ ዝንብ የማጥፋት ስራ ላይ የሚሳተፉ በፕሮጀክቱ ስር ያሉ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና በስሩ ባሉ ሶስት ጣቢያዎች ማለትም /ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ እና አርባ ምንጭን/ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

19. በተጨማሪም በቆላ ዝንብ ማጥፋት እንቅስቃሴ ላይ የባለድርሻ አካላት ማለትም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር፣ የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፣ አለም አቀፍ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎች እና የፕሮጀክቱ ሥራ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎች ተሣትፎና ቅንጅታዊ አሠራር ታይተዋል፡፡

## <u>የአሰራር ሂደት መግለጫ (Process Description)</u>

### <u>የቆላ ዝንብ ማራቢያና ማምከኛ የስራ ሂደት</u>

ከመስክ የቆላ ዝንቦችን በመሰብሰብ በአርባ ምንጭ ኢንሴክተሪ ውስጥ ማላመድ

↓

የተሰበሰቡትን የቆላ ዝንቦች ወደ ቃሊቲ ማዕከል ማጓጓዝ

↓

የቆላ ዝንብ ዕርባታ ክፍሎች ምቹ ሁኔታ እንዲኖረው ክትትል ማድረግ፣

↓

የተሰበሰቡትን የቆላ ዝንቦችቃሊቲ ማዕከል ማላመድ

↓

ብዛት ያላቸውን ሴት እና ወንድ የቆላ ዝንቦች ማራባት

↓

ወንድ የቆላ ዝንቦችን አምክኖ ጥራታቸውን በመፈተሽ

መስክ ለመልቀቅ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ

↓

የመከኑትን ወንድ የቆላ ዝንቦችን በቀረበው መረጃ መሰረት መስክ መልቀቅ

↓

መስክ የተለቀቁ የቆላ ዝንቦች ስርጭትና ውጤታማነት ክትትልና ግምገማ ማካሄድ

↓

የመካን ነፍሳት ቴክኖሎጂን በመጠቀም 25,000 ካ.ኪ.ሜ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ማጽዳትና ለእንስሳት እርባታና ለእርሻ ልማት ምቹ በማድረግ ሕብረተሰቡን በምግብ እራስን በማስቻል ማርካት፡፡

**<u>ለቆላ ዝንብ ምግብነት የሚያገለግል ደም ከብክለት ነፃ የማድረግ የስራ ሂደት</u>**

ለቆላ ዝንቦች ምግብነት የሚሆን ደም ከቄራ አሰባስቦ ማምጣት

↓

የመጣውን ደም ላብራቶሪ በማስገባት እንዳይረጋ ማስቀመጥ

↓

የደሙን ጥራት ለማወቅ ናሙና መውሰድና የባክቴሪያ መጠን መለየት

↓

ለናሙና የተወሰደውን ደም በጨረር ኃይል ከብክለት ነፃ ማድረግና ጥራቱን ማወቅ

↓

ናሙና የተወሰደበትን ደም በ2 ሊትር መያዣ ማዘጋጀትና በጨረር ኃይል ከብክለት ነፃ ማድረግ

↓

ከባክቴሪያ ነፃ የሆነውን ደም በ30 ዝንቦች ሙከራ ማድረግ

↓

ሙከራ የተደረገባቸው ዝንቦች ጥሩ ደረጃ ካሉ ሁሉም ለምግብነት አገልግሎት እንዲውል ማቀዝቀዣ ማስገባት

↓

የተዘጋጀውን ደም ለየሞጁሎቹ/ለዕርባታ ክፍሎቹ/ ማሰራጨትና ለምገባ ማዋል

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች/Findings/

### ፕሮጀክቱ በተያዘለት ዕቅድ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፣

**2.1 ፕሮጀክቱ በተዘጋጀለት እቅድ መሠረት ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው መንገድ መከናወኑንና አላማውን ስኬታማ ማድረጉን ማጣራት፣**

20. የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት በተያዘለት የዕቅድ ጊዜ (ከ1990 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም) ውስጥ የቆላ ዝንብን ከ 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ነፃ ማድረግ ያለበት ቢሆንም ከ13 ዓመታት በኋላ የተሰራው በ6,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ብቻ መሆኑን ከ2003 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡

21. በኦዲቱ በመስክ ጉብኝት ወቅት በጣቢያዎች በመዘዋወር ከባለሙያዎች ጋር በተደረገው ቃለ ምልልስ በወላይታ ሶዶና በዲላ የፕሮጀክቱ ጣቢያዎች የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ከመቀነስ ባሻገር ነፃ የሆነ አካባቢ አለመኖሩና እንዲሁም በአርባምንጭ ነፃ የሆነ አካባቢ ያለ ቢሆንም የዝንቡ መጠን ካልቀነሰበት ቦታ ለሚፈልሱ ዝንቦች መከላከያ / Barrier / ተሰርቶ የመቆጣጠር ስራ ባለመሠራቱ ከቆላ ዝንብ ነፃ ሆኖአል ለማለት የማያስችል መሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

22. የፕሮጀክቱ የጣቢያ ኃላፊዎች ይህንኑ በማስመልከት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ የወላይታ ሶዶ ኃላፊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ከመቀነስ ባሻገር ነፃ የሆነ አካባቢ አለመኖሩን፣ የዲላ ጣቢያ ኃላፊ የኬሚካልና የታርጌት አቅርቦት በበቂ መጠን ስለማይኖር ከቆላ ዝንብና ከገንዲ በሽታ ነፃ የሆነ አካባቢ አለ ለማለት የሚያስቸግር መሆኑን የገለፁ ሲሆን፣ የአርባምንጭ ኃላፊ ነፃ የሆነ ብዙ አካባቢ ቢኖርም ባሪየር/ቁጥጥር/ ተደርጐ መከላከያ እስካልተደረገ ድረስ ዝንብ እየገባ ሊወጣ ስለሚችል በትክክለኛነት መግለጽ እንደሚያስቸግር ገልፀዋል፡፡

23. እንዲሁም ስለሁኔታው የፕሮጀክቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ከ1990 ዓ.ም. እስከ 2003 ዓ.ም በ6,880 ካ.ኪ.ሜ የሚሸፍን አካባቢ ከ90-95% ከቆላ ዝንብ የመቀነስ ስራ የተሰራ መሆኑን እና ይህ ሊሆን የቻለው አንዳንድ እስከ አሁን እየተጠቀሙባቸው ባለው ቴክኖሎጂ የማይደርስባቸው አካባቢዎች የቆላ ዝንብ መሸሸጊያ በመሆን የተቀነሰባቸውን አካባቢ እንደገና በመውረርና በመበከላቸው የተነሳ ሲሆን፤ እነዚህም አካባቢዎች ፖርኮች፣

ጥብቅ ደኖች፣ ሰውና እንስሳት የሌሉባቸው፣ ለተሽከርካሪና ለእግረኛ የማያስገቡ አስቸጋሪ አካባቢዎች በመኖራቸው ምክንያት መሆኑን እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ደግሞ ከ25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ 18,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ የቅነሳ ሥራው የተጠናቀቀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

24. የ3ቱም ጣቢያዎች ኃላፊዎች እቅዱ ከአፈጻጸሙ ያነሰበትን ምክንያትን ሲገልፁ፣ የሰው ኃይል እጥረት፣ የኬሚካል እና የታርጌት አቅርቦት ማነስ፣ የሌሎች ማቴሪያል አለመሟላት እና የመሳሰሉት እንደሆኑ ከቀረበላቸው መጠይቅ እና ከመረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

25. በተመሳሳይ ሁኔታ የደቡብ ክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ስለዘገየበት ምክንያት ተጠይቀው በሰጡት ፤ ምላሽ ከዚህ ቀደም ህብረተሰቡን የባለቤትነት ስሜት ፈጥሮ አለመንቀሳቀሱ፣ የግብዓት አቅርቦት አናሳ መሆን፣ የተያዘው 25,000 ካ.ኪ.ሜ የቆዳ ስፋት ወጣ ገባና ለሥራ በጣም አመቺ አለመሆኑ ከግምት ውስጥ አለማስገባት፣ በፖርኮች ላይ የቅነሳ ስራ አለመሰራቱ እና የተጠቀሙበት ቴክኖሎጂ ውስን/ታርጌትና በከብቶች ላይ ኬሚካል መቀባት ብቻ/ በመሆናቸው ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያም እቅዱ ሲታቀድ ይህንኑ የቦታ አቀማመጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለሆነ የተሰጡትን ምክንያቶች መቀበል አልተቻለም፡፡

26. በኦዲቱ ወቅት ፕሮጀክቱ ባለፉት አስርት አመታት ጊዜ ውስጥ አላማውን ከግቡ እንዳይመታ ካደረጉት ነገሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤ ጠንካራ የማኔጅመንት ክትትል ወቅቱን ጠብቆ አለመከናወን፣ በስራ(በትግበራ ወቅት) የሚያጋጥሙ ችግሮች በግልፅ አለመገለጻቸው፣ የኬሚካሎችና የታርጌቶች/በኬሚካል ተነክሮ ለዝንቦች መከላከያ በዛፍ ላይ የሚሰቀል ጨርቅ/ ግዢ ከውጪ ሀገር ስለሚከናወን የግዢዎች መዘግየት፣ የሰው ኃይል እጥረት(የባለሙያ)፣ የማቴሪያሎች አለመሟላት በመሳሰሉት ምክንያቶች በተያዘለት እቅድ ጊዜ ግቡን እንዳይመታ ማድረጉን ከዓመታዊ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. በመሆኑም ባለፉት 10 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የተሰሩ ስራዎች በጣም አናሳ(በእቅድ ከተያዘው ያነሰ) ቢሆንም በ2003 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም እንቅስቃሴው ከበፊቱ የሚሻል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በጣቢያዎች ጉብኝት በተደረገበት ወቅት በህዳርና ታህሳስ ወር 2004 ዓ.ም አካባቢ ኬሚካሎችና ታርጌቶች በብዛት በመግባታቸው ምክንያት በወላይታ ሶዶ ሁምቦ ወረዳ አባላ ፋራቶ ቀበሌ ገበሬ ማህበር፣ አርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ፣ በሁምቦ ወረዳ ዘይሴ ወዘቃ ቀበሌ እና አባያ ወረዳ ዱቢቻ ቀበሌ በዛ ያሉ ከብቶች

1%( አንድ ፐርሰንት) ዴልታሜትሪን ለማስረጨት አርሶአደሮች ከብቶቻቸውን ይዘው አምጥተው ስራውም /ርጭቱም/ በተግባር ሲከናወን ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን በርጭቱ ወቅት አንዳንድ አርሶአደሮችን በመጠየቅ ለመረዳት እንደተቻለው የኬሚካል እርጭቱ በመከናወኑ በጣም ተጠቃሚ እንደሚያደርጋቸው፣ የርጭት ተግባሩ በአብዛኛው የሚካሄደው በ3 እና በ4 ወር አካባቢ መሆኑ፣ የኬሚካል እርጭቱ በተካሄደበት ወቅት ዝንቦች እንደሚቀንሱ ኬሚካሉ ሲጠፋ ዝንቦቹ ተመልሰው ስለሚመጡ የርጭት ተግባሩ በተከታታይ ቢያንስ በየ2 ወሩ ቢደረግ እና ዝንቦች በጣም በሚበዙበት ወቅት /ከሚያዝያ-ነሐሴ/ በየወሩ እርጭቱ ቢከናወን የሚል አስተያየት አክለው ገልፀዋል፡፡

28. በኬሚካል የተነከሩ ጨርቆች /ታርጌቶች/ አንዴ ተተክለው ለ1 ዓመት ያህል ኬሚካሉ ሳይጠፋ አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉና በ2004 ዓ.ም ኬሚካሎችና ታርጌቶች በመግባታቸው ምክንያት እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ ታርጌቶች እየተተከሉ መሆኑን ከጣቢያ ኃላፊዎች የተገለፀልን ሲሆን፤ ነገር ግን አንዳንድ አርሶአደሮች የተተከሉ ታርጌቶችን ነቅለው በመውሰድ ችግሩ እንዳይቀረፍ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ በመስክ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት ከአርባ ምንጭ የፕጀክቱ ጣቢያ ኃላፊ ጋር በተደረገ ውይይት ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. በመሆኑም በ3ቱም ጣቢያዎች የቆላ ዝንብ የመቀነስ ስራ በታቀደው መሠረት ያልተከናወነ መሆኑ፣ በተወሰነ የተሰራና በተለይ አበረታች ሥራዎች እየተሠሩ ያሉት በያዝነው በጀት ዓመት(2004) በመሆናቸው በአካባቢው የሚኖሩ ማህበረሰብም በከፊል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደረገ ቢሆንም፤ ከ25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ነፃ አለመደረጉ የአካባቢው ማህበረሰብ እንስሳቶች በገንዲ በሽታ እንዲጠቁና ከእንስሳቱ የሚገኘው ውጤትም ሆነ ለም መሬቱን ተጠቅሞ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እንዳያገኙ ከማድረጉም በተጨማሪ ሀገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንዳታገኝ ያደርጋታል፡፡

## <u>በዓመታዊ እቅድ የተያዙ ሥራዎች አፈጻጸምን በእቅዱ መሠረት የተከናወኑ ስለመሆኑ፣</u>

30. የፕሮጀክቱን ግብ ለማሳካት የሚያስችሉ ዕቅዶች በየዓመቱ ሊዘጋጁ እና ተፈጻሚነታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

31. ይሁን እንጂ በ2002 ዓ.ም እና በ2003 ዓ.ም እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ መሬት ለመሬትና የአውሮፕላን ላይ የኬሚካል እርጭት ለማከናወን በዕቅድ ቢያዝም፣ እስከ የካቲት 2004 ዓ.ም ድረስ ያልተከናወኑ መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በመጋቢት ወር 2004 ዓ.ም የመሬት ለመሬት የኬሚካል እርጭት ተግባር የተጀመረ መሆኑን በዋና ዳይሬክተሩ ቃለ ምልልስ ወቅት ተገልጾልናል፡፡ በተጨማሪም በ2002 ዓ.ም 240,000 የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን መስክ ለመልቀቅ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ እስከ የካቲት 2004 ዓ.ም ድረስ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም የእርባታ ክፍሉ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት ከመጋቢት 2004 ዓ.ም ጀምሮ የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን መስክ ለመልቀቅ በዝግጅት ላይ እንደሆኑ የክፍሉ ቡድን መሪ ያብራሩ ሲሆን በኦዲቱ የመስክ ጉብኝት ወቅት በካርቶን ለመልቀቅ የተዘጋጁትን ወንድ የቆላ ዝንቦች የታዩና በሚያዝያ 2004 ዓ.ም 158,405 የመከኑ የፋስኪፐስ ወንድ የቆላ ዝንቦች መለቀቃቸው ከሚያዝያ 2004 ዓ.ም ወርሃዊ ሪፖርት ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. ስለሁኔታው የፕሮጀክት ማእከሉ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በዕቅድ የተያዙ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ያልተሰሩበት ምክንያቶች ከዚህ በፊት በማኔጅመንት ላይ በነበሩ ችግሮች ፣ በአፍሪካ ልማት ባንክ የውጭ ሃገር ግዢ ሂደት መጓተት አሰራር እና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት መሆኑን የገለፁ ቢሆንም የተጠቀሱት ችግሮች አጥጋቢ ሆነው አልተገኙም፡፡

33. በዕቅድ የሚያዙ ስራዎች በወቅቱ ተግባራዊ የማይደረጉ ከሆነ፣ ሊተገበሩ የማይችሉ ዕቅዶች መያዛቸውን የሚያመለክቱና በዕቅድ የተያዙ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ተግባራዊ አለማድረግ፣ ፕሮጀክቱ ስራውን በተያዘለት ጊዜ እንዳያከናውን ያደርገዋል፡፡

## ለፕሮጀክቱ የተያዘለት በጀት አጠቃቀምን በተመለከተ፣

34. የፕሮጀክቱን ግብ ለማሳካት የሚያስችል የበጀት እቅድ በየዓመቱ ሊዘጋጅ እና ተፈጻሚነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
35. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት ለፕሮጀክቱ ከ1990 እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ባሉት 13 ዓመታት ውስጥ ለፕሮጀክቱ ከመንግስት የተመደበ በጀት ብር 129,518,497 ፤ ከዚህ ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው ብር 72,674,931 ሲሆን ፤ ብር 56,843,566 ወይም 43% ያህል ያልተጠቀሙበት በጀት ሆኖ ተገኝቷል፡፡
36. ፕሮጀክቱ ስላልተጠቀመበት በጀት ሁኔታ የፕሮጀክቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ፤ ማብራሪያ (ማስረጃ ሊያቀርቡልን) ሊሰጡ አልቻሉም፡፡
37. ሆኖም እኛ እንደተረዳነው ለፕሮጀክቱ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ አለመጠቀሙ ለፕሮጀክቱ በቂ ዝግጅት ያልተደረገ መሆኑን፣ የተሟላ እና ወጥ የሆነ ክትትል ባለመደረጉ ምክንያት ይህን ያህል ገንዘብ በታቀደለት መሠረት ስራ ላይ ሳይውል መቅረቱና የተፈለገውን ውጤት እንዳይመጣ አስተዋጽኦ ያደረገ መሆኑን ተረድተናል፡፡

## ለፕጀሮክቱ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ግዢ በተመለከተ፣

38. ለዕርባታ ማዕከሉና ለመስክ ስራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ መድኃኒቶች እና ኬሚካሎች ግዢ በዕቅዱ መሠረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡
39. ይሁን እንጂ በፕሮጀክት ማዕከሉ ለዝንቦች እርባታ ክፍል እና ለላቦራቶሪ እንዲሁም ለጨረር ስራ የሚያገለግል ግዢ ለማከናወን ታቅዶ ፤ ግዢዎቹ በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት አለመከናወናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡
40. በፕሮጀክቱ የግዢ ሂደታቸው ከተጀመረ ሁለት አመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው የግዢ ሂደቶች፣ ለላቦራቶሪ የሚያስፈልጉ ግዢዎች ከተጠየቁ ስድስት ወር ያለፋቸው እና ለመስክ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ማቴሪያሎች የግዢ ጥያቄ ቀርቦ ነገር ግን ግዢያቸው ያልተፈፀሙ እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል እንደዚሁም የቆላ ዝንቦች ማምከኛ እና ደምን ከባክቴሪያ ለማፅዳት የሚያገለግል ጨረር ( Industrial radiateor Gama ray ) ግዢ የተፈፀመና ነገር ግን ለኢንዱስትሪያል ራዲያተር የሚያስፈልገው ክፍል ግንባታ ያልተሰራ በመሆኑ ዕቃው ያልገባ መሆኑን በተጨማሪ ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. ግገርዎች የዘገዩበትን ምክንያት የፕሮጀክቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ በአፍሪካ ዲቨሎፕመንት ባንክ በኩል የሚከናወኑ ግገርዎች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባሰበው ጊዜ እንዳይጠናቀቅ ምክንያት እንደሆነ እና የባንኩ አሰራር የተንዛዛ በመሆኑ የውጭ ሃገር ግገርዎች ሊዘገዩ እንደቻሉና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ዕቃዎቹ የገቡ መሆኑን የገለፁ ሲሆን የሃገር ውስጥ ግገርዎችም ቢሚሉ ለክፍሎች የተሻለ አሰራር የሚፈጥሩ እንደሆነና እየተሚሉ ያሉ መሆኑን ነገር ግን ቢዘገዩም የክፍሎችን ስራ እንዲያቆሙ የሚያስገድዱ ንብረቶች አለመሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

42. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሃላፊ (ዋና ዳይሬክተር) ይህንን ይበሉ እንጂ፤ ግገርዎች ከአፍሪካ ዲቨሎፕመንት ባንክ ውጪ በሌሎች ሁኔታዎች የዘገዩባቸውን ምክንያቶች በማጣራት በቀጣይ ለሚከናወኑ ግገርዎች የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የተደረገ ጥረት ባለመኖሩ እና በተጨማሪም በሃገር ውስጥ የሚደረጉ ግገርዎችም በተያዘላቸው ጊዜ የማይጠናቀቁ በመሆኑ የፕጀክቱ ሃላፊ የሰጡትን ምክንያት ለመቀበል አልተቻለም፡፡

43. የኢንዱስትሪያል ራዲያተር ግገር የተጠናቀቀ ቢሆንም እስካሁን ሥራ ላይ ባለመዋሉ ምክንያት ያስከተለው ተፅዕኖ መኖሩን የእርባታ ማዕከሉ ኃላፊና ቡድን መሪዎች ባንድ ላይ በሰጡት ምላሽ፤ እስካሁን በመዘግየቱ ምክንያት የቆሙ ስራዎች ባይኖሩም ወደፊት የዝንቦች ቁጥር በሚጨምርበት ጊዜ የደም ማጥሪያ ሊያንስ ስለሚችል የዝንቦች እርባታ ቁጥሩ እንዳያድግ እንደሚያደርግና መሳሪያው ተገዝቶ በቅርቡ እንደሚመጣ በመጥቀስ ሲመጣ የሰራተኞችን የስራ ጫና እንደሚቀንስ፣ ጊዜ እንደሚቆጥብ፣ ብዙ ደም ራዲየት (Radiate) እንደሚደረግ፣ ስራዎች በዘመናዊና በፈጣን ሁኔታ ስለሚሰሩ የዝንቡ ቁጥር በፍጥነት ጨምሮ ከታሰበው ግብ ለመድረስ እንደሚቻልና በተጨማሪም ላለው አንድ የጨረር መሳሪያ ጫና እንዲቀንስና ከብልሽት መቀነስ ሊረዳ እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

44. ይሁን እንጂ እስከ 2002 ዓ.ም መጠናቀቅ የነበረባቸው ግገርዎች እንደ ማጠቢያ ማሽኖች፤ ዳይክሶን መደርደሪያዎች፤ ከቆሻሻ ነፃ ማድረጊያ ማሽኖች (Sterilizing Ovens) የመመገቢያ ትሪ ማጠቢያ (Tray Washing Machines)፤ ኦፕልኬተር (የኬሚካል መቀቢያዎች)፣ ሬጀንቶች፤ ማይክሮስኮፖችና ሴንትሪፌውጅ የመሳሰሉት/ እና ለላቦራቶሪ ክፍል በጣም አስፈላጊ የሆኑ እንደ/ሴንሴቲቭ ባላንስ፣ ፔትሪድሽ፣ ዲስታል፣ ኦቨን፣ ቴርሞሜትር፤ አፕልኬተር፤ ኬሚካል እና ወተርባዝ የመሳሰሉት ሊገዙ ከታቀደበት አመት የዘገዩ በመሆናቸው በዕርባታ ክፍሎች እና በላቦራቶሪዎች ስራዎች እቃዎች

በመዋዋስ ለአሰራር አመቺ ባልሆነ መልኩ እንዲሰሩ አስገድዷል፡፡ ይህም ለዝንቦች ምግብነት የሚውለውን ደም ብቃት አናሳ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## <u>የተጠናከረ የንብረት አያያዝ ስለመኖሩ፤</u>

45. በፕሮጀክት ማዕከሉ በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት የተጠናከረ የንብረት አያያዝ ሊኖር ይገባል፡፡ የንብረት አያያዙ ለስራ አመቺ በሚሆን መንገድ በቢን ካርድ ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡
46. በኦዲቱ ወቅት ለማየት እንደተቻለው በፕሮጀክት ማዕከሉ የንብረት ክፍል(መጋዘን) ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎች/በካርቶን የተቀመጡ ማይክሮስኮፖች፣ የታርጌት ጨርቶች .../ በተዘበራረቀ ሁኔታና ዕቃ ለማውጣት በማይመች መልኩ መሬት ላይ ተቀምጠው መታየታቸው፣ አንዳንድ ዕቃዎች ሳይለዩ በካርቶን እንደታሸጉ ለብዙ ጊዜ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፣ በመስክ ጣቢያዎችም በንብረት ክፍል ጥበት ምክንያት ንብረቶች በተጨናነቀ ሁኔታ መቀመጣቸው፣ ኬሚካሎችና የተለያዩ መድኃኒቶች ከተለያዩ ንብረቶች ጋር ተቀላቅለው መቀመጣቸው ፤ በተለይ በዲላ ኬሚካሎች ከነ ካርቶናቸው በቢሮ ውስጥ የተቀመጡ ሲሆን፣ በተጨማሪ ንብረቶች በውጪ/በኮርደር/ ላይ ተቀምጠው ታይተዋል፡፡
47. እንዲሁም ወረዳዎች ኬሚካሎችን ከጣቢያዎች በሚረከቡበት ጊዜ በሞዴል 22 ወጪ ተደርጐ ቢረከቡም፤ ወረዳዎች በሞዴል 19 ገቢ እና በሞዴል 22 ወጪ እንደማያደርጉና ተከታታይ ቁጥር በሌላቸው ቅጾች ገቢ እና ወጪ እንደማያደርጉ ታውቋል ታውቋል፡፡







ፎቶ፡- 1 በፕሮጀክት ማዕከሉ ንብረት ክፍል ውስዋ ንብረቶች በተዘበራረቀ ሁኔታ ተቀምጠው የሚያሳይ



ፎቶ፡- 2 በዲላ ጣቢያ በውጪ/በኮርደር/ ላይ የተቀመጡ ንብረቶች የሚያሳይ

48. ይህን በማስመልከት የደቡብ ክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ በዲላ የፕጀክቱ ጣቢያ የመጋዘን ችግር እንዳለ ጠቁመው ነገር ግን ይህ ችግር ሊፈጠር የቻለው ለስራ የተከራዩት ቤት የቀበሌ በመሆኑ መጋዘን ለመስራት ጠይው ስላልተፈቀደላቸው በየሰራተኞች ቢሮ እንዲሁም ውጪ /በቨረንዳ/ ላይ እቃዎችን ለማስቀመዋ እንደተገደዱ ገልጸዋል፡፡

49. ወረዳዎች ኬሚካል በሞዴል 19 ያልተረከቡበትን ምክንያት ሲያስረዱ ኬሚካል ከፕሮጀክት ወዋቶ ወረዳ አስተዳደር ከዚህ ወደ ሚሰራበት ቀበሌ በተዋረድ ይላካል፡፡ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ላይ በድጋሚ በሞዴል ከገባ ለአሰራር ችግር ይፈዋራል በሚል ከዚህ ቀደም የነበረውን አሰራር ይዘው የቀጠሉ መሆኑን እንደሚመስላቸው ገልጸዋል፡፡

50. የፕሮጀክት ማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ስለዚህ ጉዳይ በሰጡት ምላሽ፤ የማዕከሉን የንብረት አያያዝ በተመለከተ ጽ/ቤቱ የንብረት ማስቀመጫ የሚሆን መደርደሪያ በውጭ ሀገር የግዢ ሂደት ላይ የሚገኝና ተገዝቶ ሲገባ ችግሩ እንደሚፈታ እምነታቸው እንደሆነና እስከዚያ ግን ያሉትን ዕቃዎች በየጊዜው ዋብቅ ክትትል እየተደረገላቸው እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ የጣቢያዎችን ንብረት ክፍል(መጋዘን) በማስመልከት ፕሮጀክቱ በየጣቢያዎች የራሱ የሆኑ ጽ/ቤቶች የሌለውና ግማሹ በትብብር የተገኙ መሆናቸውንና የዲላ ጣቢያ ግን ከቀበሌ ላይ በኪራይ የተያዘና በውስጡም መለስተኛ መጋዘን ለመስራት

ቀበሌው ባለመፍቀዱ ችግሩ ከሌሎች ጣቢያዎች ጎላ ብሎ እንዲታይ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

51. በተጨማሪም ወረዳዎች ከጣቢያዎች ኬሚካል በሞዴል 19 እንደማይረከቡና የሚረከቡት ፕሮጀክቱ ባዘጋጃቸው በተዋረድ በተለያዩ ቅጾች አማካኝነት እንደሆነ እና ይህ የተደረገው መድሐኒቱ ለህብረተሰቡ በነጻ አገልግሎት ስለሚሰጥና የተቀላጠፈና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት ታስቦና የተለያዩ አካላትም ኃላፊነት እንዲወስዱ ታስቦ የተዘጋጀ እንደሚመስላቸውና ይህም የተዘጋጀው ከዚህ ቀደም በነበሩት አመራር ሲሆን፣ አዲስ የገቡትም ከዚህ ቀደም የነበረውን አሰራር ተከትለው እየሰሩና እስከአሁን ድረስ ምንም የአሰራር ግድፈት ያልታየበትና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ቁጥጥር ሊያደርጉበት የሚችል የአሰራር ስልት እንደሆነም ለማወቅ እንደቻሉ ገልፀዋል፡፡

52. ይሁን እንጂ በፕሮጀክት ማዕከሉ ንብረት ክፍል ንብረቶች በተዘበራረቀ ሁኔታ መሬት ላይ መቀመጣቸውና በቢን ካርድ ተመዝግበው አለመያዛቸው ከውጪ የሚመጡ ንብረቶች አይነታቸው ተለይቶ ለአገልግሎት ሳይውሉ እንዲቆዩ፣ እቃዎችን በመፈለግ የስራ መጓታት ማስከተል፣ ንብረቶችን ለብልሽት እንዲዳረጉ እና ንብረት ክፍሉ እንዲጣበብ ያደርጋል፡፡

53. እንደዚሁም ኬሚካሎችን ወረዳዎች ተከታታይ ቁጥር በሌላቸው ቅጾች ገቢና ወጪ ማድረጋቸው፣ ለቁጥጥር የማያመች፣ የመንግስት ንብረት አስተዳደርን ሂደት እንዳይከተል እና ያለ አግባብ ወጪ በመሆን ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

## <u>ለፕሮጀክት ማዕከሉ የሚያገለግሉ ወጥ የሆኑ የንብረት አስተዳደር እና አወጋገድ እና በስራው ላይ ተሳታፊ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መምረጫ መመሪያዎች ስለመኖራቸው፣</u>

54. ለፕሮጀክት ማዕከሉና ለመስክ ስራ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የተለያዩ መመሪያዎች፣ ደንቦችና ፎርማቶች ሊዘጋጁና ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የማይችሉ መሳሪያዎች የሚወገዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በፕሮጀክቱ ያገለገሉና የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ንብረቶች የአወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ኬሚካል የሚቀቡ ሰዎችም መምረጫ መስፈርትና ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

55. በኦዲቱ ወቅት በ3ቱም ጣቢያዎች አገልግሎት ላይ የዋሉ የኬሚካል ዕቃዎች አወጋገድ ወጥ የሆነ መመሪያ የሌለ መሆኑ፣ ጣቢያዎች እቃዎቹ አርብቶአደሩ ለሌላ አገልግሎት እንዳያውላቸው በማለት ቆራርጠው እንደሚያቃጥሏቸውና ወጥ የሆነ መመሪያ ያልደረሳቸው መሆኑ፣ በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖሩ በስራው ላይ ተሳታፊ የሆኑ ብቃት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመምረጥ የሚያገለግል ወጥ የሆነ የመምረጫ መስፈርት የሌለና ጣቢያዎች በራሳቸው ባስቀመጡት መስፈርት የሚመርጡ መሆኑ፤ ተበላሽተው ሁለት ዓመታትና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሁለት መኪኖች እና አምስት ሞተር ብስክሌቶች ካለአገልግሎት ተቀምጠው መገኘታቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. የኬሚካል ዕቃዎች አወጋገድን በተመለከተ የመስክ ኦፕሬሽን ዳይሬክተሩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለህትመት መቅረቡንና ስለአወጋገዱም ስልጠና ተሰጥቶ እና ውይይት ተደርጎ መመሪያው ለሁሉም መሰጠቱን በፅሁፍ የገለፁ ቢሆንም መረጃው ሊቀርብልን አልቻለም፡፡

57. አገልግሎት መስጠት ያቆሙ ሞተር ሳይክሎችን በተመለከተ ባለፈው አመት የተወሰኑትን ለማስጠገን ሙከራ ተደርገው ባለገራዦች ባቀረቡት ውል መሰረት ሊጠግኑ ባለመቻላቸው ሳይጠገኑ መቅረታቸውና አንዳንዶቹ በጣም ያረጁና ቤንዚን የሚበሉ በመሆናቸው ቢጠገኑ እንኳን አገልግሎታቸው ይህን ያህል እንደማይሆኑና ተጠግነው መስራት የሚችሉትን ግን ለማስጠገን ጥረት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

58. ዋና ዳይሬክተሩ ስለሁኔታው በሰጡት ምላሽ፤ የመንግስት የግዢ መመሪያ፣ የለጋሽ አካላት የግዢ መመሪያ እና ያገለገሉ ዕቃዎች አወጋገድ መመሪያ በማዕከሉ መኖሩን የገለፁ ቢሆንም፤ የንብረት አስተዳደርን መመሪያ መረጃ በተመለከተ የቀረበ ሲሆን ነገር ግን በመመሪያው መሰረት እንደማይሰራ እና የኬሚካል ዕቃ አወጋገድ መመሪያና በመስክ የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን መምረጫ መሥፈርት መመሪያ በተመለከተ መረጃ አልቀረበም፡፡

59. ሆኖም አገልግሎት ሰጥተው ወይም በተለያዩ መንገዶች የተበላሹና አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ ዕቃዎችን አወጋገድ በንብረት አስተዳደር መመሪያ ላይ ያለ ቢሆንም፤ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በንብረት ክፍል እና በእርባታ ማዕከሉ አገልግሎት መስጠት ያቆሙ የልብስ ማጠቢያዎች፣ ማይክሮስኮፖችና በጣቢያዎችም አገልግሎት መስጠት ያቆሙ ሞተር ሳይክሎች መኖራቸው፤ በተጨማሪም በወላይታ ሶዶ ለረጅም ጊዜ በመጋዘን የተቀመጠ ጥቁር የትራፕ ጨርቅ መኖሩ፣ አገልግሎት ሰጥተው ወይም በተለያዩ መንገዶች

የተበላሹና አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ ዕቃዎች በ2004 ዓ.ም የ6 ወር ሪፖርት አፈጻጸም ላይ መኖራቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠግነተው ስራ ላይ እንዲውሉ ወይም ተጠግነው አገልግሎት መስጠት ካልቻሉ የሚወገዱበት መንገድ ሳይመቻች የተቀመጡ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፤ ይህንን ለማድረግ በዓመታዊ እቅድ እና በስትራቴጂክ እቅድ ላይ ተኩረት ተሰጥቶት በዕቅድ የተያዘ አለመሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በጣቢያዎች ንብረት ክፍል ጥበት የተነሳ ዕቃዎች በመጨናነቅ ስለሚቀመጡ ጉዳት ሊደርስባቸው ስለሚችል ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡



ፎቶ፡- 3 በፕሮጀክት ማዕከሉ ውስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ኦቨኖች



ፎቶ፡- 4 በእርባታ ማዕከሉ ውስጥ ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ የማጠቢያ ማሽኖች የሚያሳይ

60. ከላይ ከተገለፁት ውስጥ በእንስሳት ጀርባ ላይ ኬሚካል የሚቀቡ የማህበረሰቡ አባላት የሚመረጡበት መስፈርት ያለመዘጋጀቱን በተመለከተ የተሰጠ መልስ የለም፡፡
ስለሆነም በፕጀሮክት ጽ/ቤቱ ያገለገሉ የኬሚካል ዕቃዎች አወጋገድ እንዲሁም በእንስሳት ጀርባ ላይ ኬሚካል የሚቀቡ የማህበረሰብ አካላት የሚመረጡበት ወጥ የሆነ መመሪያ ባለመዘጋጀቱ የኬሚካል ዕቃዎች በተለያየ መንገድ እንዲወገዱ በመደረጉ ጉዳት ሊያደርሱና ኬሚካል የሚቀቡ ሰዎችም ብቃት ያላቸው ለመሆናቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ባለመኖሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## <u>በማዕከሉ ለሚረቡ ዝንቦችና ለመስክ አገልግሎት የሚውሉ ማቴሪያሎች ስለመሟላታቸው፣</u>

61. በማዕከሉ ለሚረቡ ዝንቦችም ሆነ ለመስክ አገልግሎት የሚውሉ ማቴሪያሎች ሊሟሉ ይገባል፡፡ የተገዙ ማቴሪያሎችም ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡
62. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው በማዕከሉ ለሚረቡ ዝንቦች የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች ሳይሟሉ የእርባታ ስራን መጀመር/መስራት/ የማይቻልና የተወሰኑ እንደ ሴንሴቲቭ ባላንስ፣ ዲስትለር፣ ፔትሪዲሽ፣ አውቶ ክሌቭ፣ ቴርሞሜትር፣ አልኮል የመሳሰሉት እና ለመስክ ስራ የሚያገለግሉም እንደ ማይክሮስኮፕ፣ ኦፕልኬተር/ኬሚካል ለመርጨት የሚያገለግል/ የመሳሰሉትም እጥረት ያለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
63. ይህን በማስመልከት የመስክ ኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ የኬሚካል መርጫ መሳሪያ እጥረት መኖሩንና በፊት የነበሩትም በመበላሸታቸው የተነሳ በሶዶ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ጣቢያዎች ችግሩ በመኖሩ ግዢ ተጠይቆ ከውጭ ሀገር እስከሚመጣ ድረስ እየተጠበቁ እንደሆኑና እስከዚያው በራሱ ኬሚካሉ በሚቀርብበት ፕላስቲክ ላይ መለኪያ ስላለው እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡



ፎቶ፡- 5 በወላይታ ሶዶ አባላ ፋሪቆ ቀበሌ ያለ ኦፕልኬተር የኬሚካል ርጭት ሲካሄድ የሚያሳይ ፎቶ

64. የፕሮጀክቱ ዋና ዳይሬክተር ደግሞ ስለሁኔታው በሰጡት ምላሽ፤ ለመስክ ስራ የሚያገለግሉ አንዳንድ መሳሪያዎች ለምሳሌ Applicator, Microscope, Centrifuge & Heamatocrit heparinised capillary tube የመሳሰሉት ከዚህ በፊት የነበሩት በእርጅናና በመበላሸት፣ አንዳንዶቹም አላቂ ዕቃዎች በመሆናቸው በአሁኑ ሰዓት እጥረቱ ሊከሰት እንደቻለና ይህንንም ችግር ለመፍታት ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ የብድር ድጋፍ ግዢውን ለመፈጸም አለም አቀፍ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው ድርጅት ሐገር ውስጥ እስከሚያስገባና የጨረታውም ሂደት ረጅም ጊዜ በመውሰዱ በእርግጥ እጥረቱ ሊገጥም የቻለ ቢሆንም ችግሩን ለመፍታት ከአጋር ድርጅቶች ጋር በተለይ ከግብርና ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀትና ዕቃዎችን በውሰት በመውሰድ በስራ ላይ ከፍተኛ በደል ሳይደርስ ሥራዎችን ለማከናወን የተቻለ መሆኑንና በአሁኑ ሰዓት ዕቃዎች ከውጭ እየገቡ በመሆኑ ችግሩ ይቃለላል የሚል ግምት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

65. ሆኖም በኦዲት ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው ለእርባታ ማዕከሉ ላብራቶሪ ክፍል የሚያስፈልጉ ምንም እንኳን ስራን እስከማቆም የሚያደርሱ ባይሆኑም ለዝንቦች ምግብነት የሚውለውን ደም ጥራት ለመጠበቅ ከሚያገለግሉ ዕቃዎች ውስጥ ለምሳሌ ቴርሞሜትር እና አልኮል የመሳሰሉት እንዳልተሟሉና ለዝንቦች ምግብነት የሚውለውን ደም ከብክነት ነፃ በማድረግ ጥራቱ ካልተጠበቀ ለሚረቡ ዝንቦች የሞት አደጋ አንደኛው ምክንያት እንደሚሆንና እየሆነም እንዳለ፣ ባለ 2 ሊትር ለዝንቦች ምግብነት የሚውለውን ደም ማስቀመጫ ባለመኖሩና ባለ 1 ሊትር በመጠቀማቸው፣ ስሪንጅ ለባለ 2 ሊትር 1 ሲሪንጅ የሚበቃ ቢሆንም ለሁለት ሊትር 2 ሲሪንጅ እንዲጠቀሙና የሲሪንጅ ብክነት እንዲኖር

እንደሚያደርገው ከባለሞያዎቹ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የዝንቦች ሞት ሲከሰት ናሙና ወስዶ ለመመርመር የሚያስችል ማቴሪያል አለመኖሩና ይህም ችግሩና መንስኤው በወቅቱ እንዳይታወቅ ማድረጉን የ6 ወር ሪፖርት ግምገማ ከሠራተኛና ከባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ መረጃ ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለመስክ ስራ ከሚያገለግሉት ውስጥም የማይክሮስኮፕ እጥረት መኖሩ የገንዲ በሽታን ቁጥጥር ለማድረግ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው በመሆኑ እጥረት መኖሩ የገንዲ ህዋስ የሚገኝበትን ደረጃ ለመገምገም እንዳያስችል እያደረገው ይገኛል፡፡

66. እንደዚሁም የመሳሪያዎች እጥረት ሊከሰት የቻለው ዋነኛው ምክንያት ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ ብድር የሚገዙ ዕቃዎች ግዢ መዘግየት እንደሆነ የቀረበ ቢሆንም፤ በሀገር ውስጥ የሚገዙ የላብራቶሪ ዕቃዎች እንደ ቴርሞሜትርና አልኮል የመሳሰሉት አለመሟላታቸው ምክንያቱን ተቀባይነት እንዳይኖረው ያደርገዋል፡፡

67. በመሆኑም በእኛ አስተያየት በማዕከሉ ለሚረቡ የቆላ ዝንቦች አገልግሎት የሚውሉ ማቴሪያሎች አለመሟላት በዕርባታው ተግባር ላይ ተፅዕኖ መኖሩ፣ በላብራቶሪ የሚከናወነውን ለዝንቦች ምግብነት የሚውለውን ደም ጥራት ከብክለት ነፃ እንዳይሆንና በመስክ ስራ ላይ የሚከናወኑ ስራዎች በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት እንዳይከናወኑ ያደርጋል፡፡

## <u>ተገዝተው ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶችን በተመለከተ፣</u>

68. ለፕሮጀክቱ አገልግሎት ተገዝተው የተዘጋጁ መሳሪያዎች ለታቀደላቸው ዓላማ ሊውሉ ይገባል፡፡

69. ይሁን እንጂ በኦዲቱ፤ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ክፍል/መጋዘን/ እና በእርባታ ክፍል ውስጥ ተገዝተው አገልግሎት ሳይሰጡ አምስት አመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው አምስት ኦቨኖች፣ ሁለት የሙቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች(cold room)፣ አምስት ማይሮስኮፖች፣ አንድ የትሪ ማጠቢያ ማሽን (Sterilizer)፣ አንድ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር እና የመሳሰሉት አገልግሎት ሳይሰጡ ለረጅም ጊዜ መቆየታቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

70. በንብረት ክፍሉ ውስጥ የሚገኙ እነዚህ ንብረቶች በተለያዩ የስራ ክፍሎች እና በፕሮጀክቱ ጣቢያዎች የሚፈለጉ ሲሆን፤ ነገር ግን እነዚህን እቃዎች ጠይቀው ለተለያዩ የስራ

ክፍሎች ሳይሚሉ ለረጅም ጊዜ የቆዩ መሆናቸውን እና በንብረት ክፍል እያሉ ለስራ ክፍሎች አለመሰራጨታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

71. ሌላው የስራው ፀባይ ከሚያስፈልገው ነገሮች ውስጥ አንዱ የውሃ አቅርቦት ሆኖ ሳለ ለውሃ ማጠራቀሚያ አገልግሎት ተብሎ ከተገዛ አንድ ዓመት ያስቆጠረ የውሃ ማጠራቀሚያ በመውጫ ስብሰባ ወቅት አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል ቢባልም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አገልግሎት ላይ ሳይውል ተቀምጦ ተገኝቷል፡፡ ለዝንቦች እርባታ አገልግሎት የሚውለው Humidifier /የክፍሉን ሙቀት መቆጣጠሪያ/ውሃ ከሌለ ችግር የሚፈጥር መሆኑ፣ የዝንቦች መመገቢያና የመሳሰሉት ንፅህና ካልተጠበቀ በዝንቦች እርባታ ላይ ችግር ማስከተሉ፣ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ከተገጠመ ብዙ ዓመት የሆነውና የዛገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ የውሃ ማጠራቀሚያው ስራ ላይ አለመዋል ውሃ በጠፋ/በተቋረጠ/ ጊዜ ችግሩን የከፋ የሚያደርገውና በሚረቡ ዝንቦች ላይ ከንፅህና ጉድለትም ሆነ ከክፍሉ ሙቀት መቆጣጠሪያ የተነሳ የሞት አደጋ ሊፈጥር የሚችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡




ፎቶ፡- 6 በፕሮጀክት ማዕከሉ ለውሃ አገልግሎት ተገዝቶ ስራ ላይ ያልዋለ የውሃ ማጠራቀሚያ

72. የዕርባታ ማዕከል ውስጥ የሚገኘውን የትሪ ማጠቢያ የዕርባታ ማዕከሉን በጐበኘንበት ወቅት ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ገለጻ እንደተረዳነው ተገዝቶ አገልግሎት የማይሰጥበት ምክንያት በግልፅ ባይታወቅም እንዴት አገልግሎት እንደሚሰጥ ባለመታወቁ ምክንያት እና ተበላሽተው አገልግሎት መስጠት ያቆሙትን በተመለከተ ዕቃዎቹ ከውጪ በመምጣታቸው ስለአጠቃቀሙ የሚያውቅ የባለሞያ አለመኖር ምክንያት መሆኑን ለማወቅ ችለናል፡፡

73. የፕሮጀክት ኃላፊዎች በሠጡት ምላሽ ዕቃዎቹ በቅርቡ/በ2004/ ከውጭ የገቡ በመሆናቸው ርክክባቸው ያላለቀ መሆኑን እና የተረከቧቸው ዕቃዎችን ደግሞ የሚገጥም ባለሙያ ለማግኘት በጨረታ ሂደት ላይ እንደሚገኙና ቀሪዎቹ በቅርብ ጊዜ ስራ እንደሚጀምሩ የገለፁ ሲሆን በመውጫ ስብሰባ ወቅት የውሃ ሮቶን በተመለከተ ተገጥሞ ስራ ላይ እንደዋለ አስረድተዋል፡፡

74. የጽ/ቤቱ ሃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ በወላይታ ሶዶ፣ በአርባ ምንጭ እና በዲላ ጣቢያ የሚገኙ የፕሮጀክቶቹ ጣቢያ ኃላፊዎች የማይክሮስኮፕ እጥረት እንዳለ መግለጻቸው፤ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለዝንቦች እርባታ /Insectory/ ክፍል የሚያገለግል የዝንቦች መመገቢያ ትሪ ከባክቴሪያ ነፃ ለማድረግ የሚያገለግል የትሪ ማጠቢያ/Tray Washer/ በስራ ክፍሉ እጥረት እንዳለ ነገር ግን እቃው ቢኖርም አጠቃቀሙን የሚያውቅ ሰው ባለመኖሩ ካለአገልግሎት ከስድስት አመት በላይ መቀመጡ፣ የተለያዩ እቃዎች ከባክቴሪያ ነፃ ለማድረግ የሚያገለግሉ ኦቨኖች፣ ዝንቦች የሚመገቡት ደም ከቄራዎች ድርጅት ከመጣ በኋላ ለምግብነት እስከሚዘጋጅ ድረስ አቀዝቅዞ የሚያቆዩ ቀዝቃዛ ክፍሎች(Cold Rooms) ስራ ያልጀመሩ መሆናቸውና ለላብራቶሪ ክፍል የሚረዱ መሳሪያዎች በንብረት ክፍሉ ውስጥ እያሉ የእቃው አይነት በንብረት ክፍል ባለሞያ ባለመታወቁ አገልግሎት ሳይሰጡ መቀመጣቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ከላይ የጠቀስናቸው ማቴሪያሎች በቅርብ የገቡ ሳይሆን ከተገዙ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሲሆኑ በቅርቡ የገቡ አዳዲስ ማቴሪያሎችም እንዳሉ ታውቋል፡፡ በመሆኑም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊ የሰጡትን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

75. በነዚሁ የስራ ክፍሎች ውስጥ ከላይ የተዘረዘሩ እቃዎች ባለመሟላታቸው ምክንያት በፕሮጀክቱ ጣቢያዎች በወላይታ ሶዶ፣ በአርባ ምንጭ እና በዲላ በመሳሪያ እጥረት ምክንያት በገንዲ በሽታ የተጠቁ ከብቶችን በበቂ ሁኔታ ህክምና ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅት የተገነዘብን ሲሆን፤ በዝንብ እርባታ ክፍሎች ውስጥ ብዛት ያላቸው እቃዎች በእጅ የሚፀዱ መሆኑ፣ በላቦራቶሪ ክፍልም ንፅህናውን የጠበቀ ደም ለዝንቦች መቅረቡን ለማረጋገጥ በተወሰኑ ዝንቦች ላይ እየተሞከረ እንደሚሰራ እንጂ ሙሉ በሙሉ ደሙ የተጣራ መሆኑን በመሳሪያ ብቻ እንዳይረጋገጥ ማድረጉ እና እቃዎች በመዋዋስ እንዲፈጸሙ ከማድረጉ በተጨማሪ ስራዎች በመጠባበቅ ስለሚከናወኑ የስራ መዘግየትን እንደሚፈጥር ይታወቃል፡፡

## በማዕከሉ ለቆላ ዝንብ ዕርባታ በከፍተኛ ወጪ የተሰሩ ክፍሎችን በተመለከተ፣

76. ግንባታቸው የተጠናቀቁ የቆላ ዝንብ ማራቢያ ክፍሎች /ሞጁልስ/ ስራ ላይ በማዋል የሚያስፈልገውን የመከኑ የቆላ ዝንብ መጠንን በወቅቱ ለፕሮጀክቱ ማቅረብ ይገባል፡፡
77. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በፕሮጀክት ማዕከሉ ለቆላ ዝንብ ዕርባታ ከተሰሩት 7 ክፍሎች ውስጥ ስራ የጀመሩትም 2ቱ ብቻ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ስራ ከጀመሩትም 2ት ክፍሎች አንደኛው ክፍል ማርባት ከሚችለው አቅም በታች እየሰራ እንደሆነ ማለትም ክፍል አንድ(1) ውስጥ የሚረቡ ዝንቦች ቁጥር ከክፍል ሁለት(2) ከሚረቡት በጣም ቁጥራቸው አነስተኛ መሆኑ እና ክፍል አንድ(1) ውስጥ በዛ ያለ መሆናቸውን በእርባታ ማዕከሉ በተጐበኘበት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
78. ክፍል ሁለት ውስጥ የሚረቡ ዝንቦች ቁጥር ለምን አነስተኛ እንደሆነ የክፍሉ ቡድን መሪ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ በክፍል ሁለት የሚረቡ ዝንቦች ዓይነት ከክፍል አንድ ስለሚለዩ፣ ለማርባት በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ፣ በቫይረስ፣ በደምና በተለያየ ምክንያት የሞት አደጋ ስለሚያጋጥማቸው መሆኑን፣ የቫይረስ በሽታን ለመከላከል በደም ውስጥ የሚሰጥ መድኃኒት መጀመራቸውን እና የሞት አደጋን ለመከላከል የሚመገቡትን ደም ጥራት መጠበቅ መሆኑን በጉብኝቱ ወቅት አስተረድተዋል፡፡
79. ስራ ያልጀመሩት ክፍሎች ለምን እንዳልጀመሩ በተመለከተ ደግሞ የእርባታ ማዕከሉ ኃላፊና የክፍሎቹ ቡድን መሪዎች በጋራ የሰጡት ምላሽ የስራው ፀባይ ማቴሪያሎች ሳይሟሉ መስራት ስለማይቻል፣ ለአገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች ባለመሟላታቸው ምክንያት እና በተጨማሪ ክፍል ሶስትን በቅርብ ለማስጀመር የተገዙ ዕቃዎችም ስራ የጀመሩት ክፍሎች ዕቃ ሲበላሽ ከዚህ ለማስጀመር ከተገዙ እቃዎች በካሊቬሽን ስለሚወሰድ ክፍሉ /ሞጁሉ/ በቅርቡ ያልተጀመረ መሆኑን አስረድተዋል፡፡
80. ዋና ዳይሬክተሩም ይህን በማስመልከት የሰጡት ምላሽ ግንባታቸው የተጠናቀቁ አምስት ሞጁልስ ስራ ላይ የሚውሉት የቆላ ዝንቦች ባሉት ሁለት ሞጁሎች ከሞሉ በኋላ በሶስተኛው ውስጥ ዕቃዎች ሲሟሉ ተራ በተራ ስራ ላይ እንደሚውሉ ገልፀዋል፡፡
81. ይሁን እንጂ በእኛ አስተያየት ለዝንቦች እርባታ የሚያገለግለውን ህንፃ ለመገንባት ብር 16,988,011.86/አስራ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ አስራ አንድ ብር ከሰማንያ ስድስት ሳንቲም/ ከፍተኛ ወጪ የወጣበት ሲሆን ክፍሎቹ አገልግሎት

መስጠት ከሚጠበቅባቸው በታች እያገለገሉ የሚገኙ መሆኑን እና አምስቱ (5) ክፍሎች ሥራ ሳይጀምሩ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## የቆላ ዝንብን ለማጥፋት፤ መሬት ለመሬትና በአውሮኘላን እርጭት ለማከናወን በአካባቢ ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት ጥናት ጊዜ መውሰዱ፤

82. እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ የመሬት ለመሬት እና በአውሮኘላን ኬሚካል የመርጨት ተግባርን ለማከናወን የሚያግዝ የአካባቢ ጥናት (Environmental risk analysis) ሊደረግ እና የርጭት ተግባሩም ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

83. በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ መሬት ለመሬትና በአውሮኘላን ላይ የኬሚካል እርጭት ለማከናወን ረቂቅ የአካባቢ ጥናት (Environmental risk analysis) የተከናወነ መሆኑ ከቀረበልን መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ የኬሚካል እርጭት ዘዴ የቆላ ዝንብን ከ90-95% ለመቀነስ ከሚያገለግሉ መንገዶች አንዱ መሆኑን ከመረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

84. ይሁን እንጂ በ2003 ዓ.ም. መሬት ለመሬት እና በአውሮፕላን ኬሚካል እርጭት ለማከናወን ቢታቀድም የኬሚካል እርጭት ተግባር ከመረጃም ሆነ በመስክ ጉብኝት እስከተደረገበት እስከ የካቲት 2004 ዓ.ም ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ ታውቋል፡፡

85. ይህ ተግባር እስካሁን ያልተፈፀመበትን ምክንያት የክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመሬት ለመሬት የኬሚካል ርጭት ስራ ያልተሰራው ኘሮጀክቱ ሲጀምር የቆላ ዝንብን በኬሚካል በተነከሩ የጨርቅ ታርጌቶች፣ በትራኘ እንዲሁም በከብቶች ላይ በሚቀባ ኬሚካል ለማጥፋት እንደነበር እና በ2003 ዓ.ም ግን መሬት ለመሬት በሚረጭ ኬሚካል እና በአውሮኘላን በሚረጭ ኬሚካል ለማጥፋት ቢታቀድም ስራው ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ መወሰድ ስላለበት እርምጃ ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና ኢትዮጵያ ዱር እንስሳ ልማት እና ጥበቃ ባለስልጣን ጋር ውይይት ሲደረግ ስራው ሊዘገይ እንደቻለ ገልፀዋል፡፡ በተለይም የአውሮኘላን እርጭትን በተመለከተ በፓርኮች አካባቢ ምንም አይነት የመከላከል ሥራ ስለማይሰራ ዝንቦች ከዛ እየወጡ የፀዳውን አካባቢ ሲበክሉ እንደሚቆዩና አሁን ግን በአውሮኘላን ይረጫል የሚል ግምት እንዳላቸውና ይህን ችግር ለመፍታትም ለበላይ አካልና ለአካባቢ ባለስልጣናት በማሳወቃቸው አካባቢን ኬሚካሉ እንደማይጐዳ ከቡና

አብቃይ ቦታዎችም የራቀ መሆኑን በሙያተኛ በማስጠናት ለማሳመን ጥረት የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

86. የፕሮጀክት ማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ስለዚህ ጉዳይ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ የመሬት ለመሬትና የአውሮኘላን የኬሚካል እርጭት እስካሁን ያልተከናወኑበት ከተለያዩ ምክንያቶች ውስጥ በዋናነት ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፍቃድ ማግኘት ጋር በተያያዘ፣ በተፈጥሮ ሐብት ላይ ሊደርስ የሚችለውን የኬሚካል ብክለትና የሚያመጣውን ጉዳት ለመከላከልና ለመቀነስ Environmental and Social management plan በውጪ አማካሪ ተጠንቶ እስኪቀርብ፣ በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማሩ አንዳንድ መ/ቤቶችን ለማሳመን የተደረጉ ጥረቶች ረዥም ጊዜ በመውሰዳቸው እና እንዲሁም መሬት ለመሬት እርጭት ለማከናወን የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ከሀገር ውስጥም ከውጭም ተገዝተው መቅረብ የሚገባቸው በጊዜው ባለመቅረባቸው ሊዘገዩ የቻሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በመቀጠልም በአሁኑ ጊዜ በአውሮኘላን ለሚደረገው የኬሚካል ርጭት ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ ያለና መሬት ለመሬት የሚደረገው የኬሚካል ርጭት ባለው ቁሳቁስ ርጭቱ የተጀመረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ከሚያዝያ 2004 ዓ.ም ወርሃዊ ሪፖርት ላይ የርጭት ተግባሩ መጀመሩ ተመልክቷል፡፡

87. በመሠረቱ ዕቅዱ ከመታቀዱ በፊት ተግባራዊነቱ እንዲፋጠን የመንግሥትን ተሳትፎ ጨምሮ፣ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶች መሟላት የነበረባቸው ሲሆን ለሁለት አመታት ያህል የመሬት ለመሬትም ሆነ የአውሮኘላን ላይ የኬሚካል ርጭት ሂደት በታቀደለት ጊዜ አለመከናወኑ(መዘግየቱ) የቆላ ዝንብ ከ90-95 ፐርሰንት እንዳይቀንስ፣ የቆላ ዝንብ የማጥፋት ሂደት እንዳይፋጠን፣ የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦች መስክ እንዳይረጩ ማድረጉና የገንዲ በሽታን ስርጭት ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት የሚያጓትት ከመሆኑ በላይ በአካባቢው የሚገኙ ህብረተሰቦች ከእንስሳቱ ከሚገኝ ውጤት እና እንስሳቱን በመጠቀም ከለም መሬት ከሚያገኙት ምርት እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

## ፕሮጀክቱ በህብረተሰቡና በአካባቢው ሥነ ምህዳር ስለሚያስከትለው ጥቅምና ጉዳት በተያዘለት መርሃ-ግብር መሠረት ጥናት ስለመደረጉ፣

88. ፕሮጀክቱ በህብረተሰቡና በአካባቢው ላይ የሚያስከትለው ጥቅምና ጉዳት በተወሰኑ ዓመታት ግምገማ በማከናወን ውጤቱን በተጨባጭ መንገድ በማረጋገጥ አስፈላጊ እርምጃዎች መውሰድ ይገባል፡፡
89. ይሁን እንጂ ፕሮጀክቱ ከጀመረበት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በ1996 ዓ.ም ብቻ ለህብረተሰቡ ያስገኘውን ጥቅም በተመለከተ ጥናት የተደረገ ሲሆን፤ በመርሃ ግብሩ መሰረት በየሶስት ዓመቱ ያልተገመገመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
90. ፕሮጀክቱ እየተተገበረ ባለበት አካባቢ የሚኖሩ ህብረተሰቦች በቆላ ዝንብ መቀነስ ምክንያት ያገኙትን ጥቅም በማስመልከት የ3ቱም ጣቢያ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ ማህበረሰቡ የወተትና የስጋ ምርት በመጨመር፣ የእንስሳት ቁጥር በመጨመር፣ ያረገዙ ላሞች ውርጃ በመቀነስ፣ ለገንዲ በሽታ ህክምና ወጪ በመቀነስ፣ የእርሻ በሬ የማረስ አቅም በመጨመር በመሳሰሉት ጥቅም ያገኙ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም፤ ይህን ለማወቅ የተቻለው የማህበረሰቡን የዕለት ተዕለት የኑሮውን ለውጥ በመመልከት እንጂ ጥናት ተደርጎ የተገኘ(በጥናት የተደገፈ) አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡
91. ዋና ዳይሬክተሩም የሰጡት ምላሽ ፕሮጀክቱ ለህብረተሰቡ ያስገኘው ጥቅም በተመለከተ በ1996 ዓ.ም ጥናት የተደረገ ሲሆን ከዚያ ወዲህ ጥናት ያልተደረገ መሆኑን እና አሁን ጥናቱን በህብረተሰቡና በተፈጥሮ ሀብት ላይ ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ ለማከናወን ጥናት የሚያደርጉ ዩኒቨርሲቲዎችን ፕሮጀክቱ እያወዳደረ መሆኑን እና ጥናቱ በቅርብ ቀን ይከናወናል የሚል ግምት መኖሩን ገልጸዋል፡፡ በመቀጠልም ጥናት ማድረጉና በሰነድ መረጃዎችን መያዙ በቀላሉ ለማስረዳትና ለመግለጽ አስፈላጊ ቢሆንም፤ ዋናው ቁም ነገር ግን በመሬት ላይ ያለው እውነታ የህብረተሰቡ ምስክርነትና እየታየ ያለው ተጨባጭ ለውጥ ፕሮጀክቱ ለሕብረተሰቡ ያስገኘውን ውጤት በበለጠ እንደሚገልጹት ግምታቸውን ገልጸዋል፡፡
92. በኦዲቱ ወቅትም በ3ቱም ጣቢያዎች በተመረጡት ቀበሌዎች በተደረገው ጉብኝት ወቅት አንዳንድ አርሶአደሮች ተጠይቀው፤ ፕሮጀክቱ በ2ት ዓመት ውስጥ ለውጥ እንዳመጣላቸውና ከከብቶቻቸውም ሆነ ለም መሬትን አርሶ ከሚያገኙት ምርት ተጠቃሚ እንደሆኑ ለመረዳት የተቻለ ቢሆንም፤ ፕሮጀክቱ በቆላ ዝንብ መቀነስ ምክንያት ለማህበረሰቡ አስገኘ የተባለው ጥቅም በጥናት ተደግፎ ያለመገምገሙ በተለይም

ፕሮጀክቱ እስካሁን በህብረተሰቡና በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያስከተለው አሉታዊና አዎንታዊ ፋይዳ ተገምግሞ አለመታወቁ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ኬሚካልን መጠን አጠቃቀም በተመለከተ፣

93. ለቆላ ዝንብ ቅነሳ ስራ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች አጠቃቀም ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ የተዘረጋውም ስርዓት ተፈፃሚነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ለዚህም ለመስክ ሥራ ከህብረተሰቡ ለተመረጡት ክፍሎች ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት ተገቢው ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በመስክ ሥራ ለእንስሳት መቀቢያ የሚያገለግሉ በረቶችን በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የአካባቢውን ህብረተሰብ በማሳተፍ በየቀበሌው /በአርብቶ አደሩና በአርሶአደሩ አካባቢ/ ሊዘጋጁና ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

94. ይሁን እንጂ በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባን ኬሚካል መጠን በተመለከተ በፕሮጀክቱ የተዘረጋ ስርዓት ባይኖርም በኬሚካል አምራቹ ድርጅት በኬሚካሉ ዕቃ ላይ በፅሁፍ የተቀመጡ መስፈርቶች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በናሙና ባየናቸው 3ት ቀበሌዎች የእንስሳት የኬሚካል ርጭት ላይ ክብደታቸው ትልቅ ለሆኑ ከብቶች እስከ 20ሚሊ ሊትር፣ ክብደታቸው ትንሽ ለሆኑ ከብቶች 10 ሚሊ ሊትር እንዲቀባ እንዲሁም የቆላ ዝንቦች በጥቁር ቀለም ስለሚሳቡ ቀለማቸው ጥቁር ለሆኑ ከብቶች በዛ ያለ ኬሚካል እንዲቀቡ መስፈርት ያስቀመጠ ቢሆንም፤ ክብደታቸው አነስተኛ ለሆኑ እና ክብደታቸው ትልቅ ለሆኑ ከብቶች ተመሳሳይ የኬሚካል መጠን መጠቀማቸው፣ ቀለማቸው ጥቁር ለሆኑ ከብቶች እና ከጥቁር ውጭ ሌላ ቀለም ላላቸው ከብቶች ተመሳሳይ መጠን መቀባታቸው በተጨማሪም ከብቶችን ስርዓት ባለው መልኩ ለመቀባት የሚያስችል በረት አለመዘጋጀቱና ያሉት በረቶች በአካባቢው ካሉት ከብቶች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ከብቶችን በአብዛኛው ከበረት ውጪ በማሯሯጥ የሚቀቡ መሆኑ በኦዲቱ የመስክ ጉብኝት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡



ፎቶ፡- 7 በአርባ ምንጭ ዘይሴ ወዘቃ ቀበሌ የተለያየ

ክብደት ላላቸው ከብቶች ተመሳሳይነ የኬሚካል መጠን ሲረጩ

95. ይህን በማስመልከት የመስክ ኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ኬሚካሉ የሚረጨው ከብቶቹ ባላቸው ክብደት መጠን መሆኑን፣ በአብዛኛው ለትልልቅ ከብቶች 20 ሚሊ እና 30 ሚሊ ሆኖ እንደሚሰጥ እና ምናልባት አንዳንድ አርሶአደሮች ይህንን ስህተት ካልፈጠሩ በስተቀር በአብዛኛው ትንንሽ ጥጆች እንዲያውም መቀባት እንደሌለባቸውና ምክንያቱም የቆላ ዝንብ አብዛኛውን ጊዜ ትልልቅ ከብቶችን ስለምትመርጥና ጥጆችም ርቀው ወደ ጫካ ስለማይጓዙ እንደሆነና በከብቶች ላይ የሚረጨው ኬሚካል አንዴ የተረጨው ቢያንስ ለ1 ወር የመከላከል አቅም እንዳለው እና ይህ ርጭት በተከታታይ ያልተደረገው በግዢ መጓተት ምክንያት ረጅም ጊዜ ስለወሰደ በዚህ መሐከል ክፍተት/መቋረጥ/ ሊኖር እንደቻለና ከህዳር 2004 ዓ.ም ጀምሮ ኬሚካል እየቀረበ በመሆኑ መቆራረጥ እንደማይኖር ገልፀዋል፡፡

96. የፕጀሮክት ጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ስለጉዳዩ በሰጡት ምላሽ፤ ፕሮጀክቱ በአመት ከአንድ እስከ ሁለት ሚሊዮን የሚደርሱ እንስሳት በኬሚካል እንደሚቀቡ፣ በዚህም ምክንያት ሁሉንም ከብቶች ሚዛን ላይ እያወጡ በኪሎ ለመለየት አዳጋች በመሆኑ እና ሙያው ጠለቅ ያለ አሰራርን የሚጠይቅና ሥራው በሕብረተሰቡም ተሳትፎ ጭምር የሚከናወን በመሆኑ መጠነኛ ግድፈቶች ሊኖሩ ቢችሉም፤ ኬሚካሉ አላግባብ ጥቅም ላይ ውሏል ለማለት እንደማያስችል ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም አምራች ድርጅቱ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት በተከታታይ ለምን እንደማይቀባ ሲገልፁ፤ በከብቶች ላይ የሚቀባው ኬሚካል የጊዜውን ገደብ/Application data intervals/ በተለያዩ

ነጥቦች ላይ ጥገኛ ሊሆን/depend on many factors/ እንደሚችልና ከነዚህም መሐከል በአካባቢው ያለው የእንስሳት ቁጥር ብዛት፣ በአካባቢው የቆላ ዝንብ መጠንና አይነት፣ የአካባቢው ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ፣ የአየር ጸባይ/ዝናብ ወይስ ፀሐይ/፣ ያለው የመድሐኒት አቅርቦትና መጠን በመሳሰሉት ጥገኛ ቢሆንም መድሃኒቱ ባላቸው ጊዜ ወቅቱን ጠብቀው እርጭት እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል፡፡

97. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ቦታዎች ለትንንሽ ጥጆች እና ለትልልቅ ከብቶች የሚቀባው የኬሚካል መጠን አንድ አይነት መሆኑና ስራው እየተሠራለት ላለው ለህብረተሰብ አካል አስፈላጊው ስልጠና ባለመሰጠቱ እና ህብረተሰቡ በቂ በረቶች እንዲሰራ ባለመደረጉ ከብቶችን እያሯሯጠ በሚቀባበት ወቅት ኬሚካል ከከብቱ ጀርባ ውጭ የሚባክን መሆኑ ታይቷል፡፡

98. በዚህም ምክንያት በከብቶች ጀርባ ላይ የሚቀባው የኬሚካል አጠቃቀም ብቃት ባለው መልኩ እየተከናወነ አለመሆኑን እና የቅቢው ሂደትም የኬሚካል ብክነትን እያስከተለ መሆኑን የኬሚካል ቅቢ ሲደረግባቸው በነበሩ በወላይታ ሶዶ አባላ ፋራቶ ቀበሌ፤ በአርባ ምንጭ ዘይሴ ወዘቃ ቀበሌ እና በዲላ ዱቢቻ ቀበሌ በማየት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

99. እንደዚሁም የቆላ ዝንብ ባለባቸው አካባቢዎች የሚደረገው የኬሚካል እርጭት ወቅቱን የጠበቀ አለመሆኑን እና የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት የሚከናወን ባለመሆኑ ያካባቢው ህብረተሰብ ኬሚካሉ በሚረጭበት ወቅት ከብቶቹ በበሽታ እንደማይጠቁ እና ኬሚካሉ በዘገየ ጊዜ ዝንቦች ተመልሰው ስለሚራቡ ከብቶች በዝንቦች ተነድፈው ለገንዲ በሽታ እንዲጋለጡ እያደረገ ይገኛል፡፡

## <u>በቆላ ዝንብ የማጥፋት ስራ ላይ ለሚሳተፉ ማህበረሰብ የሚሰጡ ስልጠናዎችን በተመለከተ፣</u>

100. በቆላ ዝንብ የማጥፋት ስራ ላይ የሚሳተፉ የማህበረሰብ አካላት ስልጠናዎች ሊሰጡ ይገባል፡፡ ስልጠናዎቹም እንስሳት ላይ የኬሚካል አቀባብ፣ ታርጌት ተከላ፣ የገንዲ በሽታ አመጣጥና አወጋገድ የመሳሰሉትን ሊይዝ ይገባል፡፡ ይህንንም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የማስተባበሪያ ቢሮው ከጣቢያዎች ጋር በመተባበር እንዲሰራ መደረግ ይኖርበታል፡፡

101. በኦዲቱ ወቅት በተመለከትናቸው ወላይታ ሶዶ፣ አርባምንጭና ዲላ ጣቢያዎች ከማህበረሰብ ለተውጣጡ አካላት የሚሰጡ ስልጠናዎች እንዳሉ ቢገለፅም፤ መረጃ ተጠይቀው ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡ በተጨማሪም ስልጠናዎች በተወሰኑ ጊዜያት

የማይሰጡ በመሆናቸው ማህበረሰቡ አንዴ የሰለጠነውን በመዘንጋት ብዙ ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡

102. በታርጌት ተከላና በእንስሳት ጀርባ ላይ የኬሚካል ርጭትን በተመለከተ ለማህበረሰቡ የተሰጡ ስልጠናዎች ለመኖራቸው የተገለፀ ቢሆኑም፤ የሚሰጡት ስልጠናዎች ተከታታይነት የሌላቸውና የግንዛቤ ማስጨበጫ ለህብረተሰቡ በተለያዩ ሚዲያዎችና መንገዶች ባለመሰጠታቸው ምክንያት የዝንቡ መጠን ትንሽ ሲቀንስ ዝንቡ የጠፋ ስለሚመስላቸው ወይም መዘናጋት በመፈጠሩ ታርጌቶችን ነቅለው መውሰድ፣ ታርጌቶችን በደንብ አለመትከል የመሳሰሉት ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡

103. በሌላም በኩል በእርባታ ማዕከሉ ለሚገኙ ባለሞያዎች የሚሰጡ ስልጠናዎች እንዳሉ ከተከለሱ መረጃዎች ቢታወቅም የሚሰጡት በቂ ባለመሆናቸው የሰራተኛ ክህሎት ችግር እንዳለ እና ስልጠና እንደሚያስፈልግ ከ2004 ዓ.ም የ6 ወር የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ ታውቋል፡፡ ምንም እንኳን የውጭ ሥልጠናን በተመለከተ ከተከሰቱት ችግሮች አኳያ በመንግስት አቅጣጫ የተሰጠ መሆኑ በቃል ቢገለጽም፤ የዝንቦች እርባታ በጣም ጥንቃቄ የሚያስፈልገው እና በትኩረት ሊሰራ የሚገባው በመሆኑ የውጭ ሥልጠና በሀገር ውስጥ ስልጠናዎች/ግንዛቤ ማስጨበጫ/ ተተክቶ ለባለሞያዎች በተከታታይ ካልተሰጠ እርባታው ላይ ከፍተኛ ችግር /በዝንቦች ላይ የሞት አደጋ ቁጥር እንዲጨምር ያደርገዋል፡፡

104. ሌላው በመስክ በተመለከትንባቸው አካባቢዎች የኬሚካል ርጭት ሲካሄድ ሁሉም ከብቶች በተመሳሳይ መጠን መቀባታቸው ለሚቀቡት የማህበረሰብ አካላት ተከታታይነት ያለው ስልጠና አለመሰጠቱን ያሳያል፡፡

105. ይህንን በተመለከተ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊውን ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ኬሚካሉ የሚቀባው ከብቶቹ ባላቸው ክብደት መጠንና ትንንሽ ጥጆች የማይቀቡ ሲሆን ነገር ግን የርጭት ተግባሩን የሚያከናውኑ አርሶአደሮች የኬሚካል ርጭት ተግባሩ ላይ ስህተት ፈጥረው ካልሆነ በስተቀር ሁሉም አንድ አይነት እንደማይቀቡ ገልፀዋል፡፡

## በፕሮጀክት ማዕከሉ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ስለመኖሩ፣

106. በፕሮጀክት ማዕከሉ ለሚደረጉ የክትትልና ግምገማ ሥራ እንዲሁም ለሚደረጉ የምርምር ጥናቶች በመነሻነት የሚያገለግል የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ መረጃውም የሚረቡ ዝንቦች ቁጥር፣ በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት ለሚከሰቱ የሞት

አደጋዎች ምክንያት ተለይተው ሊወጡ እና መፍትሄ ሊወስድባቸው ይገባል፡፡ ኘሮጀክቱ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የሚገልጽ ሪፖርት፣ በማዕከሉ የሚደረጉ የፕሮጀክት ግምገማ እና የክትትል ሥራዎች የመሳሰሉትን ሊያዙና በየጊዜው ወቅታዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

107. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፤ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በዝንብ እርባታ ክፍል ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የዝንቦች የሞት አደጋ ያጋጠመ መሆኑ ቢታወቅም፤ ለመሞታቸው መንስኤ የሆኑ ጉዳዮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ተዘጋጅተው በመረጃ አለመያዛቸው በተጨማሪም በ2001 ለሙከራ የተለቀቁ ብዛታቸው 8,000 የሚሆኑ የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦች ስላስገኙት ውጤት በመረጃ ተጠናቅሮ አለመያዙ፣ የኘሮጀክት ማዕከሉ በተያዘለት 10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ዓላማውን(ግቡን) ያልመታበትን(ያላሳካበትን) ምክንያት የሚያሳይ መረጃ/ሪፖርት/፣ በየሩብ ዓመቱ የሚዘጋጁ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ በማዕከሉ ሀሙስ ሀሙስ የማራቢያ ክፍሉን በተመለከተ የሚደረግ የግምገማ ስብሰባ (ቃለጉባኤ) እና ሰኔ 2003 ዓ.ም. ስለኘሮጀክቱ ዓለም አቀፋዊ ወርክሾኘ የተደረገውን ስብሰባ የመሳሰሉት መረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡

108. በተጨማሪም በ3ቱም/በወላይታ ሶዶ፣ በአርባምንጭ እና በዲላ/ ጣቢያዎችም እያንዳንዳቸው በስራቸው የሚይዟቸው ወረዳዎች ውስጥ ያሉትን የከብት ብዛት የሚገልጽ መረጃና ለልማት ጣቢያዎችና ለወረዳዎች ስልጠና እንደተሰጠ በሪፖርቶች ቢገለጽም የተሰጠው ስልጠና ዓይነት፣ የሰለጠኑት ሰዎች ብዛት የመሳሰሉትን የሚገልጽ መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብልን አልቻለም፡፡

109. የክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ወደ መስክ በ2001 ዓ.ም የተረጩ ዝንቦችን መረጃ በተመለከተ ዝንቦቹ ተለቀው ጫካ ውስጥ ካሉ ዝንቦች ተወዳድረው ውጤታማ መሆናቸውን የሚገልጽ መረጃ ከብሔራዊ ጽ/ቤቱ ማግኘት እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡ የከብቶች ብዛት ለምን ተመዝግቦ እንዳልተያዘም የከብቶች ቁጥር መረጃ የሚገኘው በግብርና ጽ/ቤት በኩል መሆኑንና መረጃን በየጊዜው እንዲይዙ ቢጠየቁም፤ አንዳንድ የተፋለሰ መረጃዎች እንደሚቀርቡና ለወደፊቱ እንደሚስተካከል ጥረት እንደሚያደርጉ አስረድተዋል፡፡

110. ስለሁኔታው የፕሮጀክቱን ጽ/ቤት ኃላፊ ዋና ዳይሬክተር እንደ ገለፁት፤ በኘሮጀክት ማዕከሉ፣ በማስተባበሪያውና በጣቢያዎች መረጃዎች በአግባቡ እንደተያዙ ገልፀዋል፡፡

111. የፕሮጀክት ጽ/ቤት ሃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ ዝንቦች ከተቀመጠው ሳይንሳዊ የሞት መጠን ከፍ ባለ ሁኔታ በሚሞቱበት ወቅት የሞቱበት ምክንያት ተጠንቶ በመረጃ ያልተያዘ መሆኑ፣ መስክ ላይ የተለቀቁ ዝንቦች መረጃ ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንደምናገኝ ቢገለፅልንም ያልቀረበ መሆኑ፣ ባጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ መረጃ እንዲቀርቡ ቢጠየቁም አለመቅረባቸው የፕሮጀክቱ የመረጃ አያያዝ የተጠናከረ አለመሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የክትትልና የመረጃ አያያዝ በተመለከተ በሁሉም የስራ ክፍሎች ድክመት እንዳለ ከ2004 ዓ.ም የ6 ወር አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ላይ በተጨማሪ ለማወቅ ተችሏል፡፡

112. ይሁን እንጂ በእኛ አስተያየት በፕሮጀክት ማዕከሉ የተጠናከረ መረጃ ሥርዓት አለመኖሩ ችግሮች በግልጽ እንዳይታዩና ወቅታዊ መፍትሄ እንዳያገኙና ፕሮጀክቱ በሚሰራባቸው አካባቢዎች ያሉ ከብቶች ብዛት በመረጃ አለመያዙ ለየወረዳው የሚያስፈልገውን የኬሚካል መጠን እንዳይታወቅ ሊያደርግ እንደሚችል ይታመናል፡፡

## ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ስለመኖሩ፣

113. ከባለድርሻ አካላት ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት መደበኛ የሆነ መድረክ ሊኖር ይገባል፡፡ በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት ለሚከሰቱ ችግሮች ወቅታዊ የሆኑ የምርምር ስራዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መስራትና ለችግሮቹም መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የምርምር ዘዴዎች እንዲኖሩ ማድረግ ይገባል፡፡

114. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስራውን በደቡብ ክልል ሲጀምር ከክልሉ የግብርና ቢሮ ጋር በቅንጅት መስራት የሚያስችለውን የስምምነት ሰነድ በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር፣ በክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ እና በፕሮጀክቱ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ተፈርሞ በወቅቱ ከነበረው ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኮሚሽነር ይሁንታ ያገኘ ሰነድ ቢኖርም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በይበልጥ በቅንጅት መስራት ካለበት ከክልሉ ግብርና ቢሮ እና ከግብርና ሚኒስቴር ጋር መረጃዎችን የማይለዋወጥ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

115. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በዋናኝነት ከሚያከናውናቸው ስራዎች ውስጥ በሚንቀሳቀስባቸው ወረዳዎች እና ቀበሌዎች በገንዲ በሽታ የተጠቁ እንስሳትን ህክምና መስጠት ሲሆን ይህን በመረጃ በማጠናከር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በዋናኝነትም ከክልሉ የግብርና ቢሮ ጋር መረጃውን መለዋወጥ ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ስራ ከክልሉ ግብርና ቢሮ ጋር በቅንጅት ባለመሰራቱ በ2003 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖርት መሰረት

የክልሉ የግብርና ቢሮ ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ብቻ 450,000 በገንዲ የተጠቁ ከብቶች ማከሙ የተጠቀሰ ሲሆን በሌላ በኩል፤ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2003 ዓ.ም. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ ላይ ግን ለ97,625 እንስሳት የገንዲ በሽታ መድሐኒት ሕክምና መስጠቱ ገልፀዋል፡፡ ይህ የመረጃ ልውውጥ ክፍተት መኖሩን ከማሳየቱም በላይ በቅንጅት ቢሰራ ያስገኝ የነበረውን ጥቅም እንዳያገኝ ምክንያት መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የክልሉ የግብርና ቢሮ በራሱ የቆላ ዝንቦችን ለመግደል የሚያገለግል ታርጌት ተከላ የሚሰራ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

116. የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ በአዋሳ የክልሉ የእንስሳት ሀኪም የሰጡት ምላሽ የመረጃና የሪፖርት ልውውጥ ከክልል ኘሮጀክቱ ጋር እንደሚያደርጉ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የገለፁ ቢሆንም መረጃ ተጠይቀው አላቀረቡም፡፡

117. የማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ኘሮጀክቱ በሚሰራባቸው ወረዳዎች የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቀነሱንና በክልሉ ግብርና ቢሮ ለገንዲ በሽታ ህክምና ተሰጠ ተብሎ የተቀመጠው አሃዝ/450,000/ የክልሉን ሙሉ ሽፋን የሚያሳይ ሊሆን እንደሚችልና በግብርና የሚሰጠው ህክምና የላብራቶሪ ምርመራ ድጋፍን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ስህተትም ሊፈጠር እንደሚችል ገልፀዋል፡፡ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ያከናወነውን ሥራዎች ማለትም በገንዲ በሽታና የቆላ ዝንብ ቅነሳን በተመለከተ ለግብርና ሪፖርት እንደሚያደርጉና በአንፃሩ ግብርናዎች በአብዛኛው የተለያዩ ሥራዎች ስለሚሰሩና በገንዲ ህክምና ላይ ስለማያተኩሩ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ወረዳዎች የታርጌት ተከላና ቅብ በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ እንደሚደረግና የጐደለውንም ነገር እገዛና ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

118. የፕሮጀክቱ ዋና ዳይሬክተር ስለዚሁ ጉዳይ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ በወሳኝነት በቆላ ዝንብ እና በገንዲ በሽታ ላይ ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች የሚሰራው ይህ ፕሮጀክት መሆኑን እና የሚሰራውም ብቻውን ሳይሆን ከግብርና ባለሙያዎችና ከህብረተሰቡ ጋር በመሆኑ የተሰራውን የስራ ሪፖርቶች ያገኛሉ፡፡ ለክልሉም በየሩብ አመቱ ሪፖርት እንደሚያቀርቡና ከግብርና ቢሮ ግን ለፕሮጀክቱ ለገንዲ በሽታ የተሰጡ የህክምና ሪፖርቶች እንደማይቀርቡ ሆኖም ግን በፕሮጀክቱ አካባቢ በጋራ የተሰሩ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር ስራዎች ታርጌት በኬሚካል መቀባት እና ተከላ፣ በከብቶች ላይ የኬሚካል ቅቢ ግብዓቶች ከግብርና ቢቀርቡም እንኳን በተሰሩ ስራዎች ላይ የመረጃ ልውውጥ ይደረጋል፡፡ ይህ የሚሆነው እነኚህ ሥራዎች ከተሰሩ እንጂ ይህንን ሥራ የሚሰራው

ፕሮጀክቱ በመሆኑና በተጨማሪም 450,000 የሚያህል እንስሳት ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስበት አካባቢ የገንዲ ህክምና ተሰጥቷል የሚል ግምት የሌላቸውና በግብርና ጽ/ቤት የሚሰጠው የገንዲ ህክምና በአብዛኛው በላብራቶሪ ምርመራ የተደገፈ ባለመሆኑና ገንዲ ባለባቸው አካባቢዎች በግምት ህክምናው ስለሚሰጥ የታከመው ሁሉ በገንዲ በሽታ ተጠቅቶ ነው ለማለት አያስደፍርም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

119. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው ከባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ የመረጃ ልውውጥ አለመኖሩን ነው፡፡ የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ አለመኖራቸው፣ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ስራዎች በተበታተነ መልኩ መሰራታቸውን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ባለው የመረጃ ልዩነት ምክንያት ትክክለኛውን መረጃ ለማወቅ እና የገንዲ በሽታ በትክክል መቀነሱን ለመለየት አዳጋች ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

120. በተጨማሪም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት ለሚከሰቱ ችግሮች ወቅታዊ የሆኑ የምርምር ስራዎችን እንዳልተሰሩና ምንም ዓይነት የመረጃ ልውውጥ እንዳልተደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በእርባታ ወቅት የሚከሰቱ ችግሮች ግልፅ ሆነው እንዳይወጡ ከማድረጉም በላይ ለሚከሰቱት ችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሄ እንዳያገኝ እንደሚያደርገው ይታመናል፡፡

# ክፍል ሶስት

## ማጠቃለያ

3.1 **ፕሮጀክቱ በተዘጋጀለት እቅድ መሠረት ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው መንገድ መከናወኑንና አላማውን ስኬታማ ማድረጉን በተመለከተ፣**

- ፕሮጀክቱ በተያዘለት 10 ዓመት ዕቅድ ውስጥ ከ25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ የቆላ ዝንብን ነፃ ለማድረግ ቢያቅድም ክንውኑ ከ18,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ብቻ መሆኑ፣
- በፕሮጀክቱ የሚያዙ ዕቅዶች በተያዘላቢው ጊዜ የማይከናወኑ መሆኑ፣
- የፕሮጀክቱ የበጀት አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆኑና በአንፃሩም ሥራዎች በዕቅዱ መሠረት አለመፈጸማቸው፣
- የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም እንደዚሁም አወጋገድ ስርዓቱ የተጠናከረ አለመሆኑ፣
- በፕሮጀክት ማዕከሉ ለሚረቡ ዝንቦችም ሆነ ለመስክ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ መሣሪያዎችን በወቅቱ አለመሟላቱ፣
- የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት የሌለ መሆኑ፣
- ግንባታቸው ተጠናቅቆ ነገር ግን አስፈላጊ ማቴሪያሎች ባለመሟላታቸው አገልግሎት መስጠት ያልጀመሩ 5 ክፍሎች መኖራቸው፣
- የመሬት ለመሬት የኬሚካል ርጭት ተግባር ዘግይቶም ቢሆን የተጀመረ መሆኑ ነገር ግን በአውሮፕላን የሚደረገው የኬሚካል ርጭት ያልተጀመረ መሆኑ፣
- ፕሮጀክቱ ለማህበረሰቡና በአካባቢ ላይ ያስከተለው ጥቅምና ጉዳት ጥናት/የሶሽዮ ኢኮኖሚ/ በተቀመጠው መርሃ-ግብር መሠረት አለመከናወኑ፣
- በማዕከሉ አንዳንድ ያልተሟሉና ተግባራዊ ያልተደረጉ መመሪያዎች መኖራቸው፣
- እንስሳት ጀርባ ላይ ኬሚካል የሚረጩ አካላት ርጭቱን በሚያካሂዱበት ጊዜ የኬሚካል ብክነት መኖሩ፣
- ለፕሮጀክት ማዕከሉም ሆነ ለመስክ ስራ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ግዢ መዘግየት የታየባቸው መሆኑ፣

3.2 የፕሮጀክቱ ሥራ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ሕብረተሰብ የቆላን ዝንብ ለማጥፋት የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲያገኝ ስለመደረጉና የባለድርሻ አካላት ተሣታፊ ስለመሆናቸው በተመለከተ፣

- በእርባታ ማዕከሉም ሆነ በመስክ ስራ ለሚሰሩ ባለሞያዎች ተከታታይነት ያለው ስልጠና የማይሰጥ መሆኑ፣ የቆላ ዝንብ በሚኖርበት አካባቢ ላሉ የህብረተሰብ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ አለመሰጠቱ፣
- ከባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀና የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ የማይደረግ መሆኑ፣

የሚሉት ናቸው፡፡

121. በአጠቃላይ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ሲታይ እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ በበርካታ ምክንያቶች ዘገምተኛ የነበረ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አፈጻጸሙ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ ይሁንና አሁንም ቢሆን በፕሮጀክቱ የተያዙ ዕቅዶች በወቅቱ ካልተሰሩ፣ ተግባራዊነታቸውና ዘላቂነታቸው የሚያረጋግጥ ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ካልተዘረጋ ፕሮጀክቱ አሁን የያዘውንና ተጨማሪ ሊሰራ ያሰበው የ35,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ የቆላ ዝንቦችን ነፃ የማድረግ ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እሙን ነው፡፡ ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ያሻሽላሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳብ

122. **ፕሮጀክቱ በተዘጋጀለት እቅድ መሠረት ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው መንገድ መከናወኑንና አላማውን ስኬታማ ማድረጉን በተመለከተ፣**

- በኢትዮጵያ በቆላ ዝንብ ከተጠቃው 240,000 ካ.ኪ.ሜ ውስጥ በደቡብ ኢትዮጵያን የሚገኘውን 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ የቆላ ዝንብን ነፃ ለማድረግ እንዲያስችል በያዘው የ5 ዓመት ዕቅድ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተናጠልም ሆነ በጋራ ልዩ ትኩረት በመስጠት አስቸኳይ የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል፡፡ የመፍትሄ እርምጃዎቹም በእርባታ ማዕከሉም ሆነ በመስክ የሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮችን ለይቶ ማውጣትና ለችግሮቹ ከሚመለከተው አካል ድጋፍ በመጠየቅ አፋጣኝ መፍትሄ መውሰድ፣ በጉዳዩ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር መወያየትና የትብብርና የቅንጅት ስልት በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ፣ በማዕከሉ በተለይ በዕርባታ ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ባለሞያዎች እና በመስክ ስራ ለሚሳተፉ አካላት ከስራው አድካሚነት የተነሳ የሚበረታቱበት ዘዴ የመንደፍና ተግባራዊ የማድረግ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ተሳታፊ የሚሆኑበትን መንገድ የማመቻቸት ተግባራት ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- በማዕከሉ ሊተገበር የሚችል ዕቅድ የማዘጋጀት፣ በዕቅዶች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር መወያየትና የትብብርና የቅንጅት ስልት መንደፍና፣ ተገውን የአቅም ግንባታ ሥራ በመሥራት እና በዕቅድ የተያዙ ስራዎች ስለመሰራታቸው ክትትልና ግምገማ የማድረግ ሂደት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ለፕሮጀክቱ ከመንግሥት የሚመደበውን በጀት የመፈጸምና የመጠቀም አቅም ማጎልበት፣

- የፕሮጀክቱን ንብረት የመንግሥት መመሪያን በመከተል በአግባቡ መዝግቦ መያዝ፣ አጠቃቀሙንም ማሻሻልና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉትን በወቅቱ የመንግሥት ንብረት አወጋገድ ሥርዓትን ተከትሎ ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡
- በፕሮጀክት ማዕከሉ በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት የሚከሰቱ የሞት አደጋዎች ዓይነትና ለችግሩ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን በተመለከተ፣ በፕሮጀክት ማዕከሉ የእርባታ ክፍሉን በማስመልከት የሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶችና የተነሱ ችግሮችን የሚገልጹ መረጃዎች ሊያዙ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታን የሚመለከቱ መረጃዎችን አሰባስቦና አደራጅቶ ለምርምርነት ለመጠቀም እና ለሌሎች መረጃውን ለተለያየ ግብዓት ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ የሚያገኙበትም ሆነ የሚሰራጭበት መንገድ ለማመቻቸት የሚያስችል የመረጃ አያያዝና አቅርቦት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ግንባታቸው የተጠናቀቁ 5ት የቆላ ዝንብ ማራቢያ ክፍሎች በማቴሪያል ተሟልተው ስራ የሚጀምሩበት መንገድ ሊመቻች ይገባል፡፡
- የቆላ ዝንቦችን ለመቀነስ የተጀመረው የመሬት ለመሬት የኬሚካል እርጭት ተግባር ሊቀጥልና በፖርኮች አካባቢ በአውሮውፕላን ሊደረግ የታሰበው የኬሚካል እርጭት ተግባር በቅርብ ጊዜ ሊከናወን እና ስለ ተግባራዊነቱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብና አካባቢ ከፕሮጀክቱ የተገኘው ጥቅምና ጉዳት በተቀመጠው መርሃ-ግብር መሠረት በየሶስት ዓመቱ ጥናት ሊደረግና በመረጃነት ሊያዝ ይገባል፡፡ ይህም ፕሮጀክቱ የተሰሩና ያልተሰሩ ስራዎችን በደንብ ለይቶ ለማወቅና መረጃን ለበላይ አካላት ለማቅረብ ከመርዳቱም በላይ አስፈላጊውን እርምጃዎች በወቅቱ ለመውሰድ ያስችላል፡፡
- በመስክ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን መምረጫ መስፈርት/መመሪያ/ እና አገልግሎት የሰጡ የኬሚካል ዕቃዎች በተለያየ መንገድ እንዳይወገድና አንድ ወጥ የሆነ የማስወገጃ ዘዴ እንዲኖር መመሪያዎች ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው አካላት /ለጣቢያዎች/ ማሰራጨትና ስለ ተግባራዊነቱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- ኬሚካሎች የሚገዙት በውድ እና ለቆላ ዝንብ ቅነሳ ስራ ከሚያገለግሉት ውስጥ አንዱ በመሆኑ የተገዙትን ኬሚካሎች ከብክነት ለመጠበቅ አስፈላጊ መሣሪያዎችና ስለአጠቃቀሙ መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ ይህም የኬሚካል መለኪያ /Aplicator/ ሚያገለግለው መሳሪያ በብቃት በመግዛት በሁሉም ጣቢያዎች

የኬሚካል ቅቢውን በመሳሪያው ብቻ እንዲቀቡ ማድረግ፣ የርጭት ተግባሩን ከከብቶች ጋር የሚመጣጠን በረት በመስራት ከበረት ውጪ እንዳይቀቡ ማድረግ እና በርጭት ተግባሩ ላይ የሚሳተፉ የማህበረሰብ አካላትን ተከታታይነት ያለው ስልጠና በመስጠት ከብክነት መከላከል ስለሚቻል ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡

- በግዢ መዘግየት ምክንያት በዕርባታ ማዕከሉም ሆነ በመስክ ስራ ላይ ችግሮች እንዳይከሰቱ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር የሚደረጉ ግዢዎች ሊፋጠኑ ይገባል፡፡ የግዢ ሂደቶችም በሌጋሽ አካላት የሚደረጉትም በፍጥነት በመፃፍ እንዳይዘገዩና የሀገር ውስጥ ዕቃዎችም ግዢ ተጠይቆ ሳይቆዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በቶሎ ሊፈፀሙ ይገባል፡፡
- በዕርባታ ማዕከሉ የሚታዩ የመሰላቸት፣ የግዴለሽነት እና በመስክ አካባቢ የታርጌቶችን ነቅሎ መውሰድ፣ ኬሚካል በአግባቡ አለመቀባት የመሳሰሉ ችግሮችን ለማስወገድ በማዕከሉ ለሚያገለግሉ ባለሞያዎችም፣ በመስክ ስራ ላይ ለሚሳተፉና በአካባቢው ለሚኖሩ የማህበረሰብ አባላት ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ስራ ሊሰራና የተገኘው ለውጥ ላይ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣ የመስክ ኦፕሬሽን የማስተባበሪያ ቢሮ እና በስሩ ለሚገኙት 3ቱም /ወላይታ ሶዶ፣ አርባምንጭ እና ዲላ/ጣቢያዎች እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበበት የክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# <u>አባሪ 1</u>

## <u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች</u>

## <u>/EVALUATIVE CRITERIA/</u>

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ<br>/Issue/ | መመዘኛ መስፈርት<br>/Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| I. ፕሮጀክቱ በተዘጋጀለት ዕቅድ መሠረት ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው መንገድ መከናወኑንና አላማውን ስኬታማ ማድረጉን ማጣራት፣ | 1. ብቃት ያለው ወንድ የቆላ ዝንቦችን በማርባት እና በማምከን ለመስክ ስርጭት ዝግጁ ማድረግ እና የርጭት ስርዓቱ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ |
| | 2. ግንባታቸው የተጠናቀቁ የቆላ ዝንብ ማራቢያ ክፍሎች /ሞጁልስ/ ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ |
| | 3. በማእከሉ ለሚረቡ የቆላ ዝንቦች የሚቀርብ ምግብ /የከብት ደም/ ጤናማነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 4. የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦች ብቃት ሊመዘን ይገባል፡፡ |
| | 5. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ |
| | 6. በፕጀሮጀክት ማዕከሉና ከመስክ የሚላኩ ሪፖርቶች ወጥ በሆነ መልኩና ጊዜያቸውን ጠብቀው ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ |
| | 7. የቆላ ዝንብን ለመቀነስ በኬሚካል የተነከሩ ጨርቆች ወይም ለመያዝ የሚተከሉ ወጥመዶች የሚተከሉበት ዕቅድ ወጥቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 8. የፕጀክቱን እንቅስቃሴ ቀልጣፋ ለማድረግ በየሩብ አመቱ የአፈፃፀም ክትትል ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 9. የገንዲ በሽታ ከጊዜ ወደ ጊዜ መቀነሱን ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 10. የፕሮጀክቱን የስራ እንቅስቃሴ የሚያግዝ አመታዊ እቅድ ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 11. በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት ለሚከሰቱ የሞት አደጋዎች ምክንያት ተለይተው ሊወጡ እና መፍትሄ ሊወስድባቸው ይገባል፡፡ |
| | 12. በመስክ ለቆላ ዝንብ ቅነሳ ስራ የሚያገለግሉ በኬሚካል የተነከሩ ወጥመዶች ለመትከል እና እንስሳትን በኬሚካል ለመቀባት የሚያስችል ደረጃ/መስፈርት ወጥቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 13. መሬት ለመሬት ኬሚካል ለመርጨት እና እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ ኬሚካል የመርጨት ተግባርን ለማከናወን የሚያግዝ የአካባቢ ጥናት (Enviromental Risk Analysis) ሊከናወን ይገባል፡፡ |
| | 14. ለፕጀክት ማዕከሉ እና ለመስክ ስራ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የተለያዩ መመሪያዎች ደንቦች እና ፎርማቶች ሊዘጋጁ እና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ |
| | 15. በኘሮጀክቱ በዕቅድ የሚያዙ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ |
| | 16. በሶስተኛ ወገን በቅጥር የሚደረጉ ስራዎች አፈፃጸም መመሪያ ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 17. የቆላ ዝንብን በተመለከተ የመነሻ መረጃ ጥናት baseline Data Survey ሊከናወን ይገባል፡፡ |
| | 18. በፕሮጀክቱ የሚሸፈነው 25000 ካሬ ኪሎሜትር ውስጥ ያለውን የቆላ ዝንብ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊጠፋ ይገባል፡፡ |
| | 19. ፕሮጀክቱ ለህብረተሰቡ ያስገኛል የተባለውን ጥቅም ማስገኘቱ ቢያንስ በየሶስት አመቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 20. የቆላ ዝንብን ለማጥፋት መሳሪያዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡ |
| | 21. ለፕሮጀክቱ አገልግሎት ተገዝተው የተዘጋጁ መሳሪያዎች ለታቀደላቸው ዓላማ ሊውሉ ይገባል፡፡ |
| | 22. በመስክ እና በማእከሉ የሚገኙ የተበላሹ እና አገልግሎት |

| | |
|---|---|
| | መስጠት ያቆሙ መሳሪያዎች ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል:: |
| | 23. ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የማይችሉት መሳሪያዎች የሚወገዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 24. ለዕርባታ ማዕከሉና ለመስክ ስራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ መድኃኒቶች እና ኬሚካሎች ግዢ በዕቅዱ መሠረት ሊከናወን ይገባል፡፡ |
| | 25. በፕሮጀክቱ የሚከናወኑ ግዢዎች የመንግስት እና የለጋሽ አካላት የግዢ መመሪያዎች መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ |
| | 26. በፕሮጀክቱ ያገለገሉና የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ንብረቶች የአወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፧ |
| | 27. የንብረት አስተዳደር መመሪያ ሊኖር እና ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡ |
| | 28. ለፕሮጀክቱ የሚደረጉ ዕርዳታዎች በምንጭ እና በዓላማቸው ተለይተው ሊመዘገቡ ይገባል፡፡ |
| | 29. የፕሮጀክት ማዕከሉ የንብረት አያያዝን በተመለከተ የተደራጀ መረጃ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 30. ፕሮጀክቱን የሚመለከቱ የተለያዩ መረጃዎች ተጠናቅረው ሊያዙ ይገባል፡፡ |
| | 31. ፕሮጀክት ማዕከሉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የተራቡት የቆላ ዝንቦችን የተመለከተ ዝርዝር መረጃ ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| | 32. የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦች ወደ መስክ እርጭትን የተመለከተ ዝርዝር መረጃ በማዕከልም ሆነ በጣቢያ ጽ/ቤቶች በኩል ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| | 33. የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ለመከታተል በተለዩ ቦታዎች ላይ መረጃ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ |
| | 34. የገንዲ በሽታ የክትትል ስርዓትን የተመለከተ መረጃ ተጠናክሮ |

| | |
|---|---|
| | ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| II. የፕሮጀክቱ ሥራ በሚከናወን ባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ሕብረተሰብ የቆላን ዝንብ ለማጥፋት የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲያገኝ ስለመደረጉና የባለድርሻ አካላት ተሣታፊ ስለመሆናቸው ማጣራት፣ | 35. የገንዲ በሽታ አመጣጥና መከላከያውን አስመልክቶ ለአርብቶ አደሩና ለአርሶ አደሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 36. የቆላ ዝንብ በሚኖርበት አካባቢ የሚኖረው ህብረተሰብ በቆላ ዝንብ ቅነሳ ስራ ላይ በባለቤትነት ስሜት ሊሳተፍ የሚችልበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 37. ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ፣ የገንዲ በሽታ አመጣጥና መከላከያውን አስመልቶ ለመላው ህብረተሰብ በተለያየ መንገድ (በመገናኛ ብዙሃን፣ በማስታወቂያና በተለያዩ ፖስተሮች ለህብረተሰቡ) ግንዛቤ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 38. በቆላ ዝንብ ማጥፋት ሥራ ላይ የሚሳተፉት የአካባቢው ህብረተሰቦችን መምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 39. ለመስክ ሥራ ከህብረተሰቡ ለተመረጡት ክፍሎች ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት ተገቢው ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ |
| | 40. ለፕሮጀክቱ ባለሞያዎችም ሆነ ለህብረተሰቡ ስልጠና ለመስጠት የሚያገለግሉ የስልጠና ማንዋሎች ሊዘጋጁና ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 41. በመስክ ሥራ ለእንስሳት መቀቢያ የሚያገለግሉ በረቶችን በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶችን የአካባቢውን ህብረተሰብ በማሳተፍ በየቀበሌው /በአርብቶአደሩና በአርሶአደሩ አካባቢ/ ሊዘጋጁና ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ |
| | 42. በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት ለሚከሰቱ ችግሮች ወቅታዊ የሆኑ የምርምር ስራዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መስራትና ለችግሮቹም መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የምርምር ዘዴዎች እንዲኖሩ ማድረግ ይገባል፡፡ |
| | 43. ከባለድርሻ አካላት ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት መደበኛ የሆነ መድረክ ሊኖር ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 44. በፕሮጀክቱ ስር ለሚገኙ ክፍሎች የቆላ ዝንብን በተመለከተ ለምርምር የሚውሉ ግብዓቶች፣ ፅሁፎች፣ የምርምር ሪፖርቶች በፕሮጀክቱ ጽ/ቤት በላይብረሪና በመረጃ መረብ ሊቀመጡ ይገባል፡፡ |